ጻድቃንና ጠቢባን ሥራዎቻቸውም በእግዚአብሔር እጅ እንደሆኑ፣ ይህን ሁሉ እመረምር ዘንድ በልቤ አኖርሁ፤ ፍቅር ወይም ጥል ቢሆን ሰው አያውቅም ሁሉ ወደ ፊታቸው ነው፡፡

(መክ. ፱፥፩-፪)

# ስምዐ ጽድቅ



## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ

☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org

## ማውጫ

፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና ጸሐፊ
ገነት ታደሰ



የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት

# የዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ቅርምት እንዲቆም ቅዱስ ሲኖዶስ አሳሰበ

ካሳሁን ለምለሙ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይዞታ የሆኑ የዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች መቀራመት እንዲቆም ቅዱስ ሲኖዶስ ግንቦት ፲ ቀን ፳፻፲፩ ዓ.ም ባወጣው  መግለጫ አሳሰበ።

ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ነጻነት መከበር ላይ ችግር እንደሌለባት ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው ጠቅሶ አጉል ፉክክር የሚያደርጉና ከአሁን በፊት ያልነበሩ አካላት የሥርዓተ ሃይማኖት ማክበሪያ ዐደባባዮቻችንን ለመቀራመት የሚያደርጉት ጥረት ተገቢ እንዳልሆነ አስረድቷል።

ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው አያይዞም የቤተ ክርስቲያን ይዞታ የሆኑ የዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎችን ከመቀራመት ሁሉም የሚስተናገድበት የራሱ የሆነ የክብር ቦታ አግኝቶ ሊስተናገድ ካልቻለና ጉዳዩ በዚህ የሚቀጥል ከሆነ በሀገርና በሃይማኖት ተቋማት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ጠቅሶ የሚመለከተው የመንግሥት አካል ዘላቂ መፍትሔ እንዲያመጣ የተጠየቀ ሲሆን ከታሪክ፣ከነባር ባህል ጥበቃ፣ከሃይማኖት ክብርና መብት አንጻር በአንድ ቦታ ላይ ሁለት የተለያዩ ሃይማኖቶች እንዲገለገሉ ማድረግ የሚያስከትለውን ችግር በማሰብ ሌሎች የሃይማኖት ተቋማትም የመፍትሔው አካል እንዲሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪ አቅርቧል።

ቅዱስ ሲኖዶስ አክሎም በሀገራችን በቤተ ክርስቲያናችንና በምእመናን ላይ ከፍተኛ ጫና እየደረሰ መሆኑን ገልጦ "ስጋትና ጭንቀት፣አለመተማመንና ቀቢፀ ተስፋ ተንሰራፍቶ፣አብሮ ተከባብሮ ከመኖር ይልቅ ሌላውን ጥሎ ሥልጣን ለመያዝ በሚደረገው ጥረት የቤተ ክርስቲያንን መብት እየተጋፋ ምእመናንንም እያሳዘነ ነው" በማለት አስታውቋል።

በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ፈተና ውስጥ መሆኗን መዘንጋት እንደማያስፈልግ ያሳሰበው ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው በግፍ ደማቸው በየቦታው እየፈሰሰ ስላለው ምእመናን መጸለይና ያለማቋረጥ መጠየቅ እንደሚገባም ገልጧል።

መግለጫው አያይዞም "በጦርነት፣ በረኃብና በተለያዩ ግጭቶች ዋጋ እየከፈሉ ያሉት ቤተ ክርስቲያን የሥላሴ ልጅነት ሰጥታ በልጅነት ያከበረቻቸው እና እግዚአብሔር በጥብቅ አደራ ያስረከባት የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻችን ናቸው እኛ የእነርሱ ልሳን ሆንን ዛሬ ከጎናቸው ካልቆምን ነገ የእኛ አባትነት ጥያቄ ውስጥ ይገባል" ሲል አስረድቷል።

የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ራሱን ከማንኛውም አደረጃጀት ነጻ አድርጎ የሰላም ጥሪ በማሰማት ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ሰላም መረጋገጥ አጥብቆ እንደሚሠራ አሳስቦ ጉባኤው በወቅታዊ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን አሳሳቢና አስጊ ሁኔታዎች ላይ በስፋት ተወያይቶ የመፍትሔ አቅጣጫ እንደሚያስቀምጥም ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው ተጠቁሟል።

አበው "ዕርቅ ደም  ያደርቅ" እንዲሉ የዕርቅን ጥቅም በመረዳት ወደተሻለ ሰላም መምጣት እንደሚገባ ያስረዳው ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው ሕዝብን መምከርና ማስተማር እንዲሁም ወደ ዘላቂ ሰላም ማምጣት የሁሉም የሃይማኖት አባቶች ድርሻ መሆኑን አስርድቷል።

በመጨረሻም "ሰላምንና አንድነትን ለማረጋገጥ ጉልበትን እንደ አማራጭ ከመጠቀም ተቆጥበን  ችግሮችን ሁሉ በውይይትና ተቀራርቦ በመነጋገር ለመፍታት ለሚደረገው ጥረት የላቀ ድጋፍ በመስጠት በጦርነት፣በረኃብና በበሽታ እያለቁ ያሉ ወገኖቻችንን እንታደግ" በማለት ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪ አቅርቧል።




ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ



የጉባኤው ተሳታፊዎች በከፊል

# መንግሥት የዜጎችንና የእምነት ተቋማትን ደኅንነት የመጠበቅ ግዴታውን እንዲወጣ ተጠየቀ

ካሳሁን ለምለሙ

የሀገሪቱ መንግሥት የዜጎችንና የእምነት ተቋማትን ደኅንነት የመጠበቅ ግዴታውን እንዲወጣ በስልጤ ዞን ወራቤ ከተማ የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ባዘጋጀው የውይይት መርሐ ግብር ላይ ተጠየቀ፡፡

በቅርቡ በስልጤ ዞን አክራሪዎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ላይ ያደረሱትን ጉዳት ተከትሎ የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ በወራቤ ከተማ ባዘጋጀው የውይይት መርሐ ግብር የስልጤ ዞን አስተዳደር፣ ከሁሉም ወገን የተወጣጡ የሃይማኖት አባቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተገኙ ሲሆን በስልጤ ዞን ወራቤ ከተማ የደረሰውን ጉዳት ለመገምገምና መፍትሔ ለማስጠት መሆኑን በመርሐ ግበሩ ላይ በጉባኤው ከተሰጠው መግለጫ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከጥቃቱ በኋላ ከዚህ ቀደም የነበረውን የሕዝብ ለሕዝብ መልካም ግንኙነት ወደነበረበት ለመመለስ ተወያዮቹ ቃል መግባታቸውን ከመግለጫው ለመረዳት የተቻለ ሲሆን በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ጥቃት የፈጸሙ አካላት በሕግ አግባብ ለፍርድ እንዲቀርቡ እና ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ተጠይቋል፡፡

የወደሙ አብያተ ክርስቲያናት፣የምእመናን ሀብትና ንብረት መንግሥትና የአካባቢው ማኅበረሰብ በጋራ እንዲተኩ በመግለጫው የተጠየቀ ሲሆን ሕይወታቸው ላለፈ ምእመናንም ተገቢ የደም ካሣ እንዲከፈል እና የአካልና የሥነ ልቡና ጉዳት የደረሳባቸው ምእመናን ደግሞ አስፈላጊ የሆነ የሕክምና ክትትልና ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ተነግሯል፡፡ በስልጤ ዞን በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ የተፈጸመው ጥቃት መወገዙም ታውቋል፡፡

በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ፀሐፊ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ በበኩላቸው የአብሮነት ዕሴት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጉባኤው ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ ተናግረው በግለሰቦችና ቡድኖች የተጀመረን ግጭት ወደ ሃይማኖት ተቋማት መውሰድ ተገቢ እንዳልሆነ ጠቁመው ጉባኤው በውይይቱ ዘላቂ የሆነ የመፍትሔ አቅጣጫ መጠቆሙንም ተናግረዋል፡፡

# የማኅበሩ የነገ የቤት ሥራዎች

ማኅበረ ቅዱሳን ብርቱ ታዛዥ ልጅ ሆኖ በቅንነት፣ በታታሪነት፣ በአርቆ አሳቢነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግላት ሦስት ዐሠርት አመታትን አሳልፏል፡፡ የሀገሪቱን ከግማሽ በላይ የሚሸፍነውን ወጣቱን ክፍል ማእከል አድርጎ በጀመረው መንፈሳዊ አገልግሎት በርካታ የቤተ ክርስቲያንን ሥራዎች ሰርቷል፡፡ ወደ ዓለም ለመኮብለል ትንሽ የሚበቃውን፤ በአጉል እድሜ ላይ የሚገኘውን ትውልድ ከጥፋት በመታደግና ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግል መልካም ዜጋ አድርጎ በመቅረጽ ረገድ በእጅጉ ተሳክቶለታል ማለት ይቻላል፡፡

የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ለዛሬ ያደረሰውን የመጀመሪያ እርሾ (መንፈሳዊ ማኅበረ) በደንብ ተጠቅሞበት የቤተ ክርስቲያን በረከት የሆኑ ወጣቶችን በመንፈሳዊነት ወልዶና አሳድጎ ለብዙ ቁምነገር አብቅቷል፡፡ በማኅበር ደረጃ ራሱን ያሰባሰበው ወጣቱ ትውልድ ዛሬ በምናየው ትልቅ ተቋም ደረጃ ከፍ ብሎ በሀገር እና ዓለም አቀፍ ደረጃ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይበልጥ እንዲሰፋ ወጥቶ ወርዷል፤ ዛሬ ላይ ለመድረስ ብዙ መስዋዕትነት ከፍሏል፤ በተለያየ መንገድ የመጡበትን ፈተናዎች በእግዚአብሔር ኃይል ድል እያደረገ እዚህ ደርሷል፡፡ ከቤተ ክህነት እስከ ቤተ መንግሥት የነበሩበት ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች እንደ ፈሳሽ ውሃ አልፈው ሄደው ዛሬ ላይ ማኅበሩን ባለ ብዙ ታሪክ አድርገውታል፡፡

የአንድ ወጣት እድሜን ያሳለፈው ማኅበር ቤተ ክርስቲያንን በመንፈሳዊ፣ በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካው ዘርፍ በብዙ ሲደግፋት ቆይቷል፡፡ በከፍተኛ ተቋም ውስጥ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለመጡ ተማሪዎች ይሰጥ የነበረው የማህበሩ መንፈሳዊ ትምህርት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመርቀው በሚወጡበት ጊዜ በደረሱባቸው ቦታዎች ሁሉ ወንጌልን እንዲያደርሱ መሰረት ጥሏል፡፡ መንፈሳውያኑ ወጣቶች ለሥራ በሄዱበት ሁሉ የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትን በማስከፈት አገልግሎት እንዲሰጡ አድርገዋል፤ በየዐውደ ምህረቱ ወንጌል እንዲሰበክ ክርስትናው እንዲስፋፋ ከቤተ ክርስቲያን ጎን ቆመዋል፡፡ ከዚያም ባሻገር ለሥራ በተመደቡበት ቦታዎች ሁሉ በቅንነት ሀገራቸውን እንዲያገለግሉ አስችሎአቸዋል፡፡

ማኅበሩ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጎን በመቆም ሃይማኖት እንዳይበረዝ፣ የመናፍቃን እንቅስቃሴ እንዲገታ እና ምእመናን ስለእምነታቸው ጠንቅቀው አውቀው ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠብቁ ብዙ ርቀት ተጉዞ ሠርቷል፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ገዳማትና አድባራት በልማት ራሳቸውን እንዲችሉ በጉልበት፣ በእውቀትና በገንዘብ ሲደግፍ ቆይቷል፡፡ በተለይ ገጠራማ አካባቢ የሚገኙ ገዳማትና አድባራት እንዲሁም የአብነት ት/ቤቶች ለዚህ ተጠቃሽ ምሥክርም ናቸው፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን እስከ አጥቢያ አልፎም በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በተዘረጋው መዋቅሩ አማካይነት ቤተ ክርስቲያንን በማስተዋወቅ፣ ወንጌል ባልደረሰባቸው ጠረፋማ አካባቢዎች ምእመናንን በራሳቸው ቋንቋ በማስተማር፣ ከሀገራቸው ርቀው በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በወንጌል በማጽናናት ቤተ ክርስቲያንን በብዙዎች ልብ ውስጥ እንደተከለው ሁሉ ነገም በተሻለና ዘመኑን በዋጀ መልኩ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አገልግሎት ሊደግፍ ይገባል፡፡

ትላንት ባስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት ዛሬ ላይ ብዙዎችን አፍርቶ ለቤተ ክርስቲያን ትልቅ ክብር፣ ትልቅ እፎይታ መሆኑን ሁሉም ልብ ይለዋል፡፡ የብዙዎችን መንፈሳዊ ጥያቄ ለመመለስ እንዲያስችለው ወንጌልን በወረቀት እያጻፈ በየከፍተኛ ተቋማቱ በመላክ ከማስተማር አልፎ ወደ ጋዜጣ፣ መጽሔትና የቴሌቭዥን ፕሮግራም ተሸጋግሯል፡፡ በዚህ ሁሉ የወንጌል ጉዞ ውስጥ ሰዎች በተለይም የተማሪው የህብረተሰብ ክፍል በደረሰበት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን

አምባሳደር እንዲሆን አስችሏል፡፡ ሆኖም የሚቀጥሉት ዓመታት በመገናኛ ብዙኃን በመታገዝ የሚደረገው የእግዚአብሔርን መንግሥት የመስበክ እንቅስቃሴ ዘመንተኮር ፣ ከሌሎች ቴክኖሎጂውን ተጠቅመው ቤተ ክርስቲያንን እየተጻረሩ ካሉ አካላት የተሻለ በመሥራትና ቀድሞ በመገኘት የቤተ ክርስቲያንን መንጋ መጠበቅ ይጠበቅበታል፡፡

ማኅበሩ በተጓዘባቸው ሠላሳ አመታት ውስጥ ብዙ ገድሎችን ፈጽሞ እዚህ የደረሰ ቢሆንም፤ የወንጌል ጉዞ እስከ ምጽዐት ነውና ‹‹ሥራ አለብንና አንታክትም›› የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ ይዞ የቤተ ክርስቲያንን አደራ እየተወጣ ቢገኝም ትላንትን ወደኋላ ሄዶ በመመርመር፣ ሥራዎቹን በመንፈሳዊ ሚዛን በመመዘን ለነገ መበርታት፤ ከትላንት በተሻለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማገልገል ግን ይጠበቅበታል፡፡ በተለይም ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ያለችበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ከግምት በማስገባት ዘላቂ መፍትሔ መፈለግ ከማኅበሩ ሁሉም የሚጠብቀው ነው፡፡ በአባቶች ጸሎት የዘመኑን የቤተ ክርስቲያን እሾህ በዘመናዊ መንገድ በመንቀል ቤተ ክርስቲያንን የሚያሳርፍ የቁርጥ ቀን ልጅ ነውና ብርቱ ልጅነቱንም በሥራዎቹ መግለጥ አለበት፡፡

ትላንት በትንሽ ብርቱዎች የተሰራው እና ምድርን የከደነው የማኅበረ ቅዱሳን መንፈሳዊ አገልግሎት ዛሬ ላይ ባለ ብዙ መዋቅር እና ባለ ብዙ አባላት በሆነበት ጊዜ ላይ እየተካሄደ ያለውን አደራን የመወጣት አገልግሎት ሚዛን ላይ አስቀምጦ መመዘን፤ በሚዛኑ መሠረት ቀርነቱን ነቅሶ በማውጣት ችግሮቹ ላይ መስራት ተገቢም ነው፡፡ የትላንትናውን የማኅበሩን የተቀደሰ ሥራ በተደጋጋሚ ለቤተ ክርስቲያን ልጆች፣ ለምእመናን፣ ለአባቶች ማሳየት የዛሬውን የማኅበሩን ቁመና ከማስተካከል አንጻር ብዙ ይጠቅማልና እዚያ ላይ መሥራት አማራጭም ነው፡፡ በብዙ ኢመደበኛ አገልጋዮች እዚህ የደረሰው የማኅበሩ አገልግሎት ዛሬ ላይ ያለውን ቁመና መፈተሽ የነገውን ያስተካክላልና ሊታሰብበት ይገባል፡፡

ሕይወታቸው የሚመሰክር፣ ኑሯቸው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የሆኑ የብዙ አባላት ባለቤት የሆነው ማኅበረ ቅዱሳን የዛሬዎቹንም አገልጋዮች ዞር ብሎ ማየት መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እና የግል ሕይወታቸውን ማስተዋል ከመንፈሳዊ አገልግሎቱ ጎን ለጎን አጥብቆ ሊሰራበት ይገባል፡፡ ባልተለወጠ ማንነት የእግዚአብሔርን ቤት ማገልገል ከቶም አይቻልምና ማኅበሩ የአባላቱ መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ አጥብቆ መሥራት ይኖርበታል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ለመደገፍ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ለማሳለጥ የሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ከቶም ጥያቄ ውስጥ መግባት የሌለበት አጀንዳ ነውና በቀጣይ አመታት ውስጥ ትልቅ ቦታ ሰጥቶ መስራት ይጠበቅበታል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ትላንት ባለተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲመች አድርጎ ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ ነገ ደግሞ በአንጻራዊነት የተሻለ ጊዜ ነውና የተሻለ መንፈሳዊ አገልግሎትን ብዙዎች ከእርሱ እንደሚጠብቁ አስቦ መሥራት ተገቢ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከትላንቱ መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ የሚያስተምሩትን በመውሰድ፤ ጋሬጣ የነበሩትን ነቅሶ በማውጣት የትላንት ታታሪ የቤተ ክርስቲያን ልጅነቱን ጠብቆ በመጓዝ የቤተ ክርስቲያንና የቅዱሳን አባቶቻችን መንፈሳዊ ኩራትነቱን አስጠብቆ በጥንቃቄ መጓዝ ዘመኑ የሚጠይቀው ነው፡፡

# በውስብስብ ፈተና ውስጥ ያለፉ ሠላሳ የአገልግሎት ዓመታት

ካሳሁን ለምለሙ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ አንስቶ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌልን ለሰው ልጆች ሁሉ በማድረስ ምድራዊና ሰማያዊ አገልግሎት እየሰጠች ትገኛለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን ልጆቿ በሥጋወ ደሙ ተወስነው የክብሩ ቀዳሽ የመንግሥቱ ወራሽ እንዲሆኑ ለዘመናት ያልተከለሰና ያልተበረዘውን ወንጌል ለምእመናን ጆሮ ስታደርስ ቆይታለች፡፡ ይህንን የተረዱና የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ለመደገፍ በግል ተነሳሽነት ወስደው ካለፉት ዓመታት ወዲህ ቊጥራቸው ቀላል የማይባል መንፈሳዊ ማኅበራት ተመሥርተዋል፡፡ መንፈሳዊና ሀገራዊ ድርሻዋን በመደገፍ በኩል ጎልተው ከታዩ ጥቂት መንፈሳዊ ማኅበራት መካከል ደግሞ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ መዋቅር ሥር እንዲተዳደር ቅዱስ ሲኖዶስ ዕውቅና የሰጠችው ማኅበረ ቅዱሳን ነው፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በቅንነት እንዲያገለግል ዕውቅና ከተሠጠው ጊዜ ጀምሮ በብዙ ፈተናዎችና ውጣ ውረዶች እየተፈተነ ላለፉት ፴ ዓመታት የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት የሚያግዝ ትውልድን የሚያንጽ እውነተኛ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ባለፉት ፴ የአገልግሎት ዓመታት የገጠሙትን ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች ተቋቁሞ አሁንም ድረስ ትውልድን የሚያንጽና ቤተ ክርስቲያንን ከሁለተናዊ ችግር የሚያድን ሥራ እየሠራ ይገኛል፡፡

ላለፉት ሠላሳ ዓመታት ማኅበረ ቅዱሳን ኃይለ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርጎ ባከናወናቸው መንፈሳውያት ተግባራት ወጣቱ ትውልድ በሥነ ምግባር የታነፀና ሀገሩንና ወገኑን የሚወድ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ የማይተካ ድርሻ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ለመበረዝ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ነጣቂ ተኵላዎችን በማጋለጥ፣ በምእመናን ላይ ግንዛቤ በመፍጠርና ቤተ ክርስቲያን ውስጣዊ፣ ውጫዊ፣ አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጥቃት ተጋላጭ እንዳትሆን የልጅነት ድርሻውን ሲወጣ የቆየ ማኅበር ሲሆን ቤተ ክርስቲያናችንም ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ፈተናዎች በሚያጋጥሟት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርጎ ከአባቶች መመሪያና ትእዛዝ በመቀበል ለችግሮች ሁሉ ዘመኑን የዋጀና የችግሩን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ የመፍትሔ ሐሳብን በማቅረብ መንፈሳዊና ሕጋዊ ርምጃዎች እንዲወሰዱ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል፡፡

ማኅበሩ ከ ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ጀምሮ በቅዱስ ሲኖዶስ ዕውቅና አግኝቶ አገልግሎቱን በይፋ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ድፍን ፴ ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ማኅበሩ የተመሠረተበት ዘመን ‹‹ሃይማኖት አያስፈልግም›› የሚል ሥርዓተ መንግሥት በነበረበት ወቅት በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን፣ የአገልጋዮችንና የምእመናን ህልውና አደጋ ላይ በወደቀበት ዘመን በመንፈሳዊ ቁጭት የተመሠረተ መሆኑ ልዩና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የማይተካ ድርሻ ያለው መሆኑን ሁሉም አካል ይረዳል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለመላው ዓለም ተዳርሶ ትውልድ በምግባር ታንጾ ከጥፋት ተመልሶ ማየት ዋና ዓላማው አድርጎ ላለፉት ፴ ዓመታት ፍጹም መንፈሳዊ የሆነ አገልግሎት ሲያከናውን የቆየ ሲሆን የያዝነውን ዓመት በሙሉ ፴ኛ ዓመት የምሥረታ በዓሉን የተለያዩ መንፈሳዊ መርሐ ግብራትን በማዘጋጀት እያከበረ ይገኛል፡፡ መርሐ ግብራቱ ማኅበሩ ላለፉት በርካታ ዓመታት ያከናወናቸውን መንፈሳዊ ተግባራት ለመግለጥ እንዲሁም የቀጣይ የአገልግሎት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለምእመናን፣ ለባለድርሻ አካላትና ለአጋር አካላት ለማጋራት ታልመው የተዘጋጁ ሲሆን መርሐ ግብራቱ በዋናነት ማኅበረ ቅዱሳን ባለፉት ፴ ዓመታት ያሳለፋቸውን የገልግሎት ሂደቶች ለመገምገምና ለቀጣይ አገልግሎት የሚረዱ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመለየት፣ በተጨማሪም ተተኪ አገልጋዮችን ለማፍራትና የማኅበሩን የአገልግሎት ውጣ ውረድ ለማሳወቅ ታሳቢ ተደርገው የተዘጋጁ መርሐ ግብራት ናቸው፡፡

የማኅበረ ቅዱሳንን ፴ኛ ዓመት የአገልግሎት ጉዞ ዓመቱን ሙሉ ለመዘከር ሲታሰብ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተነድፈው እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ከመርሐ ግብሩ አዘጋጅ ዐቢይ ኮሚቴ መረዳት ተችሏል፡፡ ዐውደ ርእይ፣ ዐውደ ጥናት፣ ዘጋቢ ፊልም፣ መጽሐፍ ዝጅትና የክብረ በዓል ዝግጅቶች ከፕሮጀክቶቹ መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ፕሮጀክቶቹን እውን ለማድረግ ዐቢይ ኮሚቴው ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ እንዲሰበስብ ኃላፊነት ወስዶ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡ የማኅበሩን ፴ኛ ዓመት የአገልግሎት ጉዞ መርሐ

ግብር እውን ለማድረግ ከላይ የተጠቀሱት ፕሮጀክቶች የላቀ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ በዚህ ዓመት ሁሉም ተግባራዊ የሚሆኑት ፕሮጀክቶች ማኅበሩ በቀጣይ ለሚፈጽማቸው አገልግሎቶች የማይተካ ሚና ስለሚኖራቸውና መሠረት ለመጣል ስለሚያግዙ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ በዐቢይ ኮሚቴው ጥሪ ቀርቧል፡፡

የማኅበረ ቅዱሳን ዋና ጸሓፊ ዋስይሁን በላይ ከማኅበረ ቅዱሳን ብሮድካስት አገልግሎት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት ማኅበረ ቅዱሳን በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ሥር በቅዱስ ሲኖዶስ ዕውቅና አግኝቶ በይፋ አገልግሎቱን ከጀመረ ፴ ዓመታትን ማስቆጠሩን ገልጠው ባላፉት ፴ ዓመታት የማይቻሉ የሚመስሉ አገልግሎቶችን ቢፈጽምም የቀሩና ገና ያልደረሰባቸው የአገልግሎት ዘርፎች እንዳሉ አስረድተዋል፡፡

ዋና ጸሓፊ በነበራቸው ቆይታ በማኅበሩ በኩል መሠራትና መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮችን መለየታቸውን አስረድተው ከዚህ ቀደም የተሠሩ መልካም ሥራዎችን ለማስቀጠልና ያልተሠሩ ሥራዎችን በመንፈሳዊ ቁርጠኝነት ለማከናወን እንዲያግዝ የማኅበሩን የ፴ ዓመት የአገልግሎት ጉዞ በውጭና በሀገር ውስጥ ባሉ ማእከላት፣ወረዳ ማእከላትና ግንኙነት ጣቢያዎች በተለያዩ መርሐ ግብራት ታስቦ እየዋለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ባለፉት ፴ ዓመታት በማኅበረ ቅዱሳን የአገልግሎት ጉዞ ከፍተኛ ድጋፍ ሲያደርጉ የቆዩ መደበኛና ኢ መደበኛ አገልጋዮች በተዘጋጁት መርሐ ግብራት በሙሉ ምስጋናና ዕውቅና እንደቸራቸው አክለው ተናግረዋል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን በልጅነት መንፈስ ላለፉት ፴ ዓመታት የማይቻሉ የሚመስሉ አገልግሎቶችን ሲፈጽም ቢቆይም ያልፈጸማቸውና ገና ያልደረሰባቸው አገልግሎቶች እንዳሉ ከዋና ጸሓፊው መረዳት እንደቻልነው ማኅበሩ ከሚሠጠው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች በተጨማሪ በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን እየፈተናት ያለውን የአፀራረ ቤተ ክርስቲያን የፀጥታ ስጋት ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ቤተ ክርስቲያንን፣ ኦርቶዶክሳውያንና ሀገርን ሊያስቀጥል የሚችል ሥራ ለመሥራት ማኅበሩ ከዚህ ቀደም የነበሩበትን የአገልግሎት እንከኖች በማረምና ተግባራዊ የሚሆን ከምን ጊዜው የተሻለ ስልታዊ ዕቅድ በመንደፍ የቤተ ክርስቲያንን የአገልግሎት ችግር መቅረፍና የመከራ ጊዜን ማሳጠር ያስፈልጋል፡፡ በማኅበሩ የ፴ ዓመት የአገልግሎት ጉዞው ውስጥ ውጣ ውረድ ሲያዩ ለነበሩ አገልጋዮች ዕወቅናና ምስጋና መቸር ደግሞ ሌሎች በትሩፋት ሊያገለግሉ የሚችሉ ወገኖችን በቀላሉ ለማግኘ አጋዥ መሆኑን መርዳት ያስፈልጋል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እያለፈ ለዘለዓለማዊ ሕይወት የሚያበቃውን እውነተኛ የሃይማኖት ትምህርት እያስተማረ ያለ ተቋም ሲሆን ገዳማት፣ አድባራትንና የአብነት ትምህርት ቤቶች ሲቋቋሙም በሙያና በገንዘብ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ትውልዱ ሃይማኖቱን ጠንቅቆ ያወቀ በሥራና በምግባር የታነፀ እንዲሆን ከማድረግ አኳያም የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

ምእመናን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ወንጌልን እንዲማሩና እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ከማድረጉም ባሻገር ከእያንዳንዱ ማኅበረሰብ የወጡ ወጣቶችን በመመልመል ተከታታይ ሃይማኖታዊ ሥልጠና በመስጠት ተመለሰው ወገኖቻቸውን በቋንቋቸው እንዲያገለግሉ እያደረገ ይገኛል፡፡ ከአካባቢያቸው፣ ከወገን ዘመዳቸው ርቀው የተወሰኑ ዓመታትን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያሳልፉ ኦርቶዶክሳውያን ወጣት ተማሪዎች እንዲሁ ከእግዚአብሔር እንዳይርቁ፣ በወንጌል ጥማት እንዳይቸገሩና አፅናኝ እንዳያጡ ግቢ ጉባኤያትን አቋቁሞ ተማሪዎች በፈለጉት ጊዜ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲያገኙ እያደረገ ሲሆን ባለፉት ፴ የአገልግሎት ዓመታት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች የራሳቸውንና የሌሎችን መንፈሳዊ ሕይወት ቀይረዋል፡፡ ምእመናን በዐውደ ምሕረት ከሚያገኙት የወንጌል አገልግሎት ባሻገር በየትም ቦታና ሰዓት ውስጥ ሆነው እውነተኛ የክርስቶስ ወንጌልን እንዲማሩ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን ሲጠቀም ቆይቷል፡፡

በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ ዘርፉ አገልግሎቱ የላቀ ድርሻ ያለው ማኅበሩ በተለይ በጠረፋማ አካባቢዎች ላይ በሚሰጠው የወንጌል አገልግሎት ባህላቸውን ሃይማኖት አድርገው ለዘመናት የቆዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አስተምሮ በማስጠመቅ የከበረውን የሥላሴ ልጅነት እንዲያገኙ አድርጓል፡፡ እነዚህ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች አምነው ተጠምቀው የሥላሴ ልጅነትን ያገኙት አብዛኛዎቹ ከደቡብና ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሲሆኑ በሌሎች አንዳንድ የሀገራችን ክፍሎችም መሰል አገልግሎቶችን እየፈጸመ ይገኛል፡፡ ሰዎች አምነው ተጠምቀው የሥላሴ ልጅነትን እንዲያገኙ የማድረግ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ያሉ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ጸንተው ሌሎችን እንዲያጸኑ ያለመ ሲሆን ሌሎች ያላመኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አሳምኖ የሥላሴ ልጅነትን እንዲያገኙ ማድረጉ ዘለዓለማዊ በሆነ የቅድስና ሕይወት እንዲመላለሱ አድርጓቸዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የማኅበረሰባችንን የኑሮ ችግር እንደአጋጣሚ በመጠቀም የተለያዩ የእምነት ተቋማት በገጠርና በጠረፋማ አካባቢ ያሉ ወገኖችን በጥቅም

በመደለል የተሳሳተ ትምህርት እያስተማሩ መሆኑን ማኅበሩ ተረድቶ ሥራዎችን ሲሠራ የቆየ ሲሆን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከእናት ቤተ ክርስቲያን የተለዩ ምእመናንን እንዲሁ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዲመለሱ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ጥረቱም ውጤት አምጥቶ ብዙዎቹ ከተከሉዋቸው ነጠቃ ድነው በእናት ቤተ ክርስቲያን ሥር ሆነዋል፡፡ የእናት ቤተ ክርስቲያንን ጣዕም ቀምሰው ነገር ግን በነዋይ ተታለው ከቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት መድረክ ርቀው የቆዩ አገልጋዮች በቀኖና ዐውደ ወደ ምህረት እንዲመለሱ ማኅበሩ የራሱን ድርሻ ተወጥቷል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን በትሩፋት የሚያገለግሉ በርካታ ካህናት፣ ዲያቆናት ሰባክያነ ወንጌል ማፍራቱን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በየዓመቱ ከግቢ ጉባኤያት ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች በሀገሪቱ ባሉ አንዳንድ የካህናት ማሠልጠኛ ተቋም ገብተው በመሠልጠን በስብከተ ወንጌል አገልግሎት ተሰማርተው ቤተ ክርስቲያንነ እያገለገሉና ትውልዱን በመልካም ሥነ ምግባር እያነፁ መሆኑን የማኅበሩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በውጭው ዓለምም እንዲሁ ማኅበሩ ማእከላትን በማቋቋም ኦርቶዶክሳውያን ባሉበት ሀገራት ሁሉ የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን እንዲስፋና ከሀገራቸው ርቀው በባዕድ ሀገር ያሉ ምእመናን እንዲጽናኑ ላለፉት ሠላሳ ዓመታት ያልተቋረጠ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ሲከውን መቆየቱ ይታወቃል፡፡ እነዚህንና በዚህ ጽሑፍ ያልተገለጡ አገልግሎቶችን ሲፈጽም ነገሮች አልጋ በአልጋ ሆኖለት ሳይሆን እጅግ ከባድ በሆነ ፈተና ውስጥ እያለፈ መሆኑን በተለያዩ ጊዜያት በሰማናቸውና ባየናቸው ሁሉ መረዳት ችለናል፡፡

የማኅበረ ቅዱሳን መሥራችና የ፴ኛ ዓመት ክብረ በዓል ዝግጅት ዐቢይ ኮሚቴ ዋና ሰብሳቢ ቀሲስ ዶክተር ሙሉጌታ ሥዩም ከማኅበረ ቅዱሳን ብሮድካስት አገልግሎት ጋር በነበራቸው ቆይታ ማኅበሩ ባሳለፋቸው ፴ የአገልግሎት ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ ፈተናና ጫና ያሳልፍ እንደነበር አስረድተው በዚህም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሲሉ በርካታ የማኅበሩ አገልጋዮች "ሰማዕት በመሆን የክርስቶስ ሙሽሮች ሆነዋል" ሲሉ ተናግረዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ፈተና በጠነከረበት ወቅት አገልጋዮች በቅናተ ቤተ ክርስቲያን ተነሳስተው በግልም ሆነ በቡድን ተደራጅተው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የበለጠ ዋጋ ለመክፈል ይንቀሳቀሱ እንደነበር ያስረዱት ቀሲስ ዶክተር ሙሉጌታ ሥዩም የማኅበረ ቅዱሳን የምሥረታ መነሻም በቤተ ክርስቲያን ላይ ይፈጸም የነበረው በደል እንደነበር ተናግረዋል፡፡ ይፈጸም የነበረውን በደል ከተቻለ ለማስቀረት ካልተቻለ ደግሞ ለመቀነስ ማኅበሩ ጥረት ያደርግ እንደነበር አክለው አስረድተዋል፡፡

የማኅበረ ቅዱሳን ፈተና የጀመረው ገና ከምሥረታው ጀምሮ ነው፡፡ ፈተናዎቹ ከውስጥና ከውጭ የመነጩ ነበሩ፡፡ ማኅበሩ በተመሠተበት ወቅት አባቶችን ማገዝ፣ ቤተ ክርስቲያንን መታዘዝ ሳይሆን የራሱን ድብቅ ተልእኮ ይዞ ሊቃውንትን ለማሳደድ፣ ለቤተ ክርስቲያን በማዳከም አስተዳደሩን ለመረከብ የሚመስላቸው ሰዎች ሲያደርሱት የነበረው መከራ ቀላል አልነበረም (ሐመር መጽሔት ግንቦት ፳፻፲፬ ዓ.ም ገጽ-፲፱)፡፡ አፅራረ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናት ማኅበሩን በአክራሪነት መነጽር በማየት ከፍተኛ የሆነ ጫና ከማሳደራቸው በተጨማሪ አንዳንድ ጊዜም የአገልግሎት እንቅፋት ሲሆኑ ይስተዋሉ ነበር፡፡ በተለያዩ ጊዜያት የማኅበሩ መደበኛና ኢ-መደበኛ አገልጋዮች በተለያዩ የመንግሥት አካላት ወከባና እንግልት ሲደርስባቸው ቆይቷል፡፡ እንኳን መንፈሳዊ ሥራዎችን የሚሠራ ማኅበር ይቅርና ዓለማዊ ሥራዎችን የሚሠራም በፈተና ውስጥ ማለፍ ግድ መሆኑን ማኅበሩ ተረድቶ በወጀብና በመአበል ውስጥ እያለፈም ቢሆን ለሀገርና ለትውልድ የሚበጀውን ከመሥራት ለአፍታም ቢሆን አልተገታም፡፡ ማኅበሩ ለችግሮቹ ሁሉ ወቅታዊና አስፈላጊ የሆኑ መፍትሔዎችን እያስቀመጠ ትውልዱ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ተኮትኩቶ እንዲያድግ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲሰፋ፣ የቤተ ክርስቲያን መብትና ክብር እንዲጠበቅ፣ ሥርዓትና ዶግማዋም እንዳይበረዝና እንዳይከለስ በርካታ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል፡፡

ማኅበሩ ለሚገጥሙት ፈተናዎች እግዚአብሔርን አጋዥ ደርጎ የተለያዩ መፍትሔዎችን እያበጀ በማለፍ እዚህ ደረጃ የደረሰ ቢሆንም ውስጣዊ ፈተናዎቹ ከውጫዊ ፈተናዎቹ የበለጡ እጅግ አድካሚና ውስብስብ በመሆናቸው ችግሮችን በቀላሉና በአጭሩ ለመፍታት ሲቸገር ቢቆይም በአንጻራዊነት ለአገልግሎት እምብዛም እንቅፋት ሲሆኑ አይስተዋልም፡፡ ውስጣዊ ችግሮቹን ለመፍታት አስቸጋሪ የሚያደርገው በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ውስጥ ያሉ አካላት የችግሩ አባባሾች በመሆናቸው ነው፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ላለፉት ፴ ዓመታት ያገኘውን የአገልግሎት ጥንካሬ በማስቀጠል በቀጣይ የተለመደና ከዚህ ቀደም ከነበረው የአገልግሎት ሱታፌ የተሻለ አገልግሎት እንደሚፈጽምና የምእመናንና የቤተ ክርስቲያን አለኝታ ሆኖ እንደሚቀጥል ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ማኅበሩ የክርስቶስን ወንጌል ለመላው ዓለም ለማዳረስ እያደረገ ካለው ጥረት በተጨማ የቤተ ክርስቲያናችን ውስጣዊ የአሠራር ችግሮች እንዲስተካከሉና ቤተ ክርስቲያን የአሠራር ችግር ሳይኖርባት ለትውልድ እንድትተላለፉ እገዛ እንደሚያደርግ ሙሉ እምነት በመጣል የቤተ ክርስቲያንን ክብርና መበት የሚጥሱ የውስጥና የውጭ ኃይሎችንም ጭምር እንደሚታገላቸው ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ልዑል እግዚአብሔር የማኅበራችን የአገልግሎት ዘመን ይባርክልን፡፡ አሜን!!!

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር*** !

# የተማሩና ጸሎተኛ የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች ለማቃለል ዕለት ዕለት የሚተጉ ታላቅ አባት

ክፍል አንድ

**በካሳሁን ለምለሙ**

በጣም ደፋር፤ ግልፅ፤ፊት ለፊት የሚናገሩ፤ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚመሩ ምእመናን፣ ጠንክረው ሥራ ለሚሠሩና ለተገፉ ወገኖች ሁሉ የሚወግኑ፤ ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ አካላትን በድፍረት የሚጋፈጡ እና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣አስተምህሮና መብት የማይደራደሩ አባት፤ ከራሳቸው ይልቅ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዕለት ዕለት የሚጨነቁ፤የተበላሸን ለማስተካከል የማይቦዝኑ፤ኑሯቸውን በመተው ራሳቸውን ለአገልግሎት አሳልፈው የሰጡ እውነተኛና ቅን አባት መሆናቸውን በርካታ የአገልግሎት በልደረቦቻቸው ይመሰክሩላቸዋል፡፡

ከሰዎች ደስታ የማይለዩ በኃዘናቸው ደግሞ የሚያጽናኑ እንዲሁም ካላቸው ላይ ሳይሆን ከሌላቸው ላይ ለተቸገረ ሰው የሚያካፍሉ፣ በዚህ ሥራቸውም የደግነትና የርኅራኄ አባት መሆናቸውን አስመስክረዋል፡፡ በመንፈሳዊ አባትነት ሁሉንም ሰው እኩል የሚያቀርቡ፣የሚመክሩ፣የተጣላን የሚያስታርቁ ከሥጋዊ ሕይወት ይልቅ ለመንፈሳዊ ሕይወት ቅድሚያ የሚሰጡ ነበሩ፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ከእግዚአብሔር እንዳይርቁ፣ ቤተ ክርስቲያንን አጥብቀው እንዲወዱና በቅንነት እንዲያገለግሉ የመከሩ ያስተማሩ አባት መሆናቸውን ያስመሰከሩ ናቸው፡፡

ከግል ዝናና ምቾት ይልቅ ዕለት ዕለት ስለቤተ ክርስቲያን ደኅንነትና አንድነት የሚጨነቁ አባት በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያንን ቀረ በማይባል ሁኔታ በቅንነትና በታማኝነት እስከ ዕድሜ ፍጻሜአቸውድረስ ሲያገለግሉ ኖረዋል፡፡ በአገልግሎት ዘመናቸው ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉና ስለቤተ ክርስቲያን ደኅንነት አብዝተው የሚጨነቁ ብዙ ወጣት አገልጋዮችን አፍርተዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋትን ሁሉ ያበረከቱ አባትም ነበሩ፡፡ ሰዎች በቃሉ አምነውና በክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ታትመው እንዲኖሩ ባደረጉት ጥረትም በርካቶች በጋብቻ



መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ

ተወስነው በየጊዜው ከአምላካቸው ጋር እየተነጋገሩ እንዲኖሩ የቀደመውንና የሚያስፈልገውን እውነተኛ መንገድ እንዲከተሉ አሳይተዋል፡፡ የእኒህ አባት የአገልግሎት ዘመን በሥጋ ድካም ዕረፍት ተገታ እንጂ በሕይት ቢቆዩ ኖሮ ከዚህ የበለጠ አገልግሎት መፈጸም እንደሚችሉ ከአገልግሎት ዘመናቸው መረዳት ይቻላል፡፡ በዕድሜ ማምሻ በሚመጣ አካላዊ ድካምና ሥጋዊ ዕረፍት የተነሣ አባታችን ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ከዚህ ዓለም ተለይተዋል፡፡ የተከበራችሁ አንባብያን የዛሬው የቤተ አብርሃም ዐምድ እንግዳችን መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ ይባላሉ፤ የርሳቸው የአገልግሎትና የሕይወት ተሞክሮ ያስተምራል ይመክራል ብለን በማሰብ በሚከተለው መልኩ ተሪካቸውን አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ በቀድሞ አጠራር ትግራይ ክፍለ ሀገር አድዋ አውራጃ ሓሓይለ ወረዳ ከአባታቸው መልአከ ምሕረት

ገብረአምላክ ኃይሉ (በዘመኑ ታዋቂ ሊቃውንት የነበሩ) እና ከእናታቸው እማሆይ ፀሐዬቱ ተድላ ግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ተወለዱ። መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስቅዱስ ገብረ አምላክ የዘር ሐረጋቸው ከአክሱም፣ከጎንደር፣ ከላስታና ሸዋ የሚመዘዝ ማንነት ያላቸውና ከልጅነታቸው ጀምሮ ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን ጠብቀው የኖሩ እውነተኛ የሕዝብና የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ አባት ነበሩ። መልአከ ብርሃናት ዘመንፈ ስቅዱስ የልጅነት ጊዜአቸውን በወላጆቻቸው ቤት በደስታና በእንክብካቤ ያሳለፉ ሲሆን በመጀመሪያ የቃል ትምህርታቸውን ከወላጅ አባታቸው ከመልአከ ምሕረት ገብረአ ምላክ ኃይሉ ዘንድ ተምረዋል።

ቀለም ገብ እና ትምህርት ቶሎ ተቀባይ መሆናቸውን የተረዱት ወላጅ አባታቸው በወቅቱ በአካባቢው ታዋቂ መምህር ለነበሩት መምህር ወልደ ኤዎስጣቴዎስ ኪዳኑ ሰጥተዋቸው የወላጆቻቸው ክትትልና እንክብካቤ ሳይጓደልባቸው ትምህርታቸውን መከታተል ጀመሩ። መሠረታዊ ነገረ ሃይማኖት፣ውዳሴ ማርያምና አንቀጸ ብርሃንን ከወላጅ አባታቸው መልአከ ምሕረት ገብረ አምላክ ኃይሉ የተማሩ ሲሆን፣ንባብ፣ ቅዳሴና ዜማ ደግሞ ከመምህር ወልደ ኤዎስጣቴዎስ ኪዳኑ እና ከመሪጌታ ገብረ እግዚአብሔር ተምረው ለአገልጋይነት የሚያበቃቸውን ዕውቀት ቀስመዋል። መልአከ ብርሃናት ዘመንፈ ስቅዱስ በአባታቸው እጅግ በጣም ተወዳጅ ልጅ ስለነበሩ አባታቸው የአስተዳደርና የዳኝነት ሥራዎችን በቅርበት እየተገኙ እንዲከታተሉና ልምድ እንዲቀስሙ ያደርጓቸው ነበር። አባታቸው ለአገልግሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱም አብረዋቸው እንዲሄዱ ያደርጉ ስለነበር ለአገልግሎት መትጋትንና የአገልጋይነት ስሜትን ጠንቅቀው እንዲማሩ አድርገዋቸል።

በልጅነታቸው በአካባቢያቸው ቅርብ የሚባል ዘመናዊ ትምህርት ቤት ባለመኖሩ የቅርብ ቤተሰባቸው ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ባርያጋብር (በወቅቱ የአክሱም ንቡረ ዕድ፣ የአድዋ አውራጃ ገዢ፣ እና የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ካቢኔ አፈጉባኤ) የነበሩ በአዲስ አበባ ከተማ ጃንሜዳ አካባቢ በነበረው ቤታቸው ቤተሰቦቻቸውን ሰብስበው እያስተማሩ መሆናቸውን ስለተረዱ ለመማር ይናፍቁት የነበረውን ዘመናዊ ትምህርት ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ስላደረባቸው በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም ከሌሎች እኩያ የቅርብ ዘመዶቻቸው ጋር በመሆን በእግር ተጉዘው አዲስ አበባ ከተማ በመምጣት ከደጃች ገብረ ሥላሴ ባርያጋብር ቤት ሆነው መማር ጀመሩ። ትምህርታቸውን በጥሩ ሁኔታ ጀምረው በደጃዝማቹና በቤቱ ሹማምንት ከፍተኛ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገላቸው ሳለ ወላጅ አባታቸው ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር በሄዱበት ወቅት በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ዐረፉ። መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ የአባታቸውን ሞት በሕልማቸው አይተው ስለነበረ “አባቴ ሞተዋልና ወደሃገሬ ልመለስ” ብለው ለደጃዝማቹ ጥያቄ ሲያቀርቡ ደጃዝማች ገብረሥ ላሴም ብላቴናው ባየው ሕልም እርግጠኛ መሆኑ እንዳስገረማቸው ሕይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ ነገሩን ያስታውሱት ነበር። በዚያ ወቅት በአባታቸው ዕረፍት ምክንያት ወደ ትውልድ አካባቢያቸው እንዲሄዱ ተፈቅዶላቸው ስንቅ ተዘጋጅቶላቸው ተላኩ። በወቅቱ የአባታቸው ሥርዓተ ቀብር የተፈጸመው በድንገት በሞቱበት ጎንደር ክፍለ ሀገር ነው።

የዲቁና መዓርግ ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወኵሎን አድያማተ ትግራይ ቀደም ሲል የተቀበሉት ወጣት ቤተ ክርስቲያንን በተማሩት ትምህርት እያገለገሉ በአባታቸው ዕረፍት ምክንያት የተበተነውን ርስትና ቅርስ ለማስከበር ኃላፊነት ወሰዱ። ከዚህ ቀደም ከወላጅ አባታቸው የቀሰሙትን ዕውቀትና የሙግት ችሎታ በመጠቀም የቤተሰባቸውን ሀብትና ርስት አስከብረዋል። በዚያ የልጅነት ዕድሜያቸው ያሳዩትን ድፍረት፣ትጋትና ንቃት የተመለከቱ በርካቶች አርአያ ያደርጓቸው ነበር። ይህንን ያዩት ደጃዝማች ገብረ ኢየሱስ እና ደጃዝማች ገብረ ማርያም የእኅታቸውን ልጅ ዳሯቸው።

መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ በ፲፱፻፵፬ ዓ.ም ሥርዓተ ጋብቻቸውን በደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ይተዳደር በነበረው በደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዓዲዕራእ በሥርዓተ ተክሊል ፈጽመው ለስልሳ ዓመታት ያህል በሕግ ጸንተው ኖረዋል። መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ ጋብቻቸውን ከፈፀሙ በኋላ መዓርገ ቅስና ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወኵሎን አድያማተ ትግራይ ተቀብለው አገልግሎታቸውን ጀምረዋል። ከክህነት አገልግሎታቸው በተጨማሪ

ያስተዳድሯቸው የነበሩ አድባራት ሰፋፊ ርስቶች የነበራቸውና የተለያዩ ችግሮች የነበሩባቸው በመሆናቸው ችግሮቹን በመፍታትና ርስቶቹን በማስከበር ረገድ ከፍተኛ አገልግሎት እንደፈጸሙ ይነገራል። ያስተዳድሯቸው የነበሩ አድባራትን እስከ ኅልፈተ ሕይወታቸው ድረስ ችግሮቻቸውን በመፍታት፤ንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍትን በማሟላት፤ እንዲሁም የልማት እንቅስቃሴያቸውን የመደገፍ አገልግሎት ሰጥተዋል። መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ በነበራቸው ንቃት፣ ትጋትና ልዩ አስተዳደራዊ ችሎታ በአድዋ አውራጃ ከጭቃ ሹምነት ጀምሮ እስከ ሀገር ገዥነት ተሹመው አገልግለዋል።

መልአከ ብርሃን ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ ከትግራይ ወደ አዲስ አበባ የመጡት በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ሲሆን የመጡትም አዲስ አበባ የሚገኙ ቤተ ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ነበር። ብዙ ቤተሰቦቻቸው ከሚገኙበት ቀበና አካባቢ እየተነሡ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ጸሎት ያደርሱ ነበር። የተለመደ ጸሎታቸውን በሚያደርሱበት በአንዱ ቀን የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሰላማ ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም በመጡበት ወቅት በአንደኛው በር አጠገብ ቆመው ቅዳሴ ማርያም በቃል የሚደግሙትን ቄስ ዘመንፈስ ቅዱስን አገኟቸው። ብፁዕነታቸው የሚያደርሱትን ጸሎት እስኪጨርሱ ጠብቀው ራሳቸው ጠርተው አናገሯቸው። በዚያው ዕለት ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ይዘዋቸው በመሄድ በወቅቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ከነበሩት ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ጋር አገናኟቸው። ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛውም የብፁዕ አቡነ ሰላማን ምስክርነት ከተቀበሉና ስለማንነታቸው ከራሳቸው አንደበት ከተረዱ በኋላ በዘመኑ ከፍተኛ በሚባል ደመወዝ (አርባ ብር) በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ገዳም በቅስና ተመድበው እንዲያገለግሉ ከተመደቡ በኋላ የገዳሙ ዋና አስተዳዳሪና የመንፈሳዊ ኮሌጁ ዲን ከነበሩት ሊቀ ሥልጣናት አባ ኃይለ ማርያም ወርቅነህ (በኋላ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ) ጋር አገናኝተው ላኳቸው።

መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ በአዲስ አበባ ከተማ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተመድበው ባገለገሉበት ወቅት ታዋቂና ምስጉን ለመሆን ጊዜ አልፈጀባቸውም። በዘመኑ አስፈላጊ የነበረውን ሰበካ ጉባኤ የማደራጀትና ምእመናን ግዴታቸውን እንዲወጡ ማድረግ፤አባልነታቸውን በወቅቱ እንዲያድሱ በማድረግና ያደሱና ያላደሱ የንስሓ ልጆቻቸውን ለይተው በመያዝ ረገድ የሚያሳዩት አፈፃፀም የታላላቅ አብያተ ክርስቲያናትን መሪዎች ትኩረት የሳበ በመሆኑ ሊቀ ሥልጣናት አባ ኃይለ ማርያም ወርቅነህና ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው በልዩ ሁኔታ ይቀርቧቸውና ይከታተሏቸው ነበር። ወቅቱ ቤተ ክርስቲያን የነበራት ሀብት ንብረት የተወረሰበት፤ ሰበካ ጉባኤ ያልተጠናከረበት እና ቤተ ክርስቲያን ሁለገብ መዳከም ውስጥ የነበረችበት ወቅት ስለነበር በጣም ለተጎዱ አጥቢያዎች ምእመናንን በማስተባበር ንዋያተ ቅርድሳትና ቅዱሳት መጻሕፍትን ማሟላት የታወቁበት ሥራ ሆነ። ከመንበረ ታቦት ጀምሮ እስከ ቀንዲልና መቁረርት ሁሉንም ማሟላት የቻሉ እውነተኛ አባት ነበሩ። በዚህ ተግባራቸው ብዙ ሳይቆዩ በትጉህ አገልጋይነታቸው ተመረጠው ሽልማቶችን ከተለያዩ አካላት ተቀብለዋል። መልአከ ብርሃን ዘመንፈስ ቅዱስ በግብዝና ተመርጠውም መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን አጠናክረዋል። በዚህም በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም በታማኝ አገልጋይነታቸው ተመርጠው ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እጅ ካባ፤ ሙሉ እጀ ጠባብ፣ የሀር ልብስ (የባህል ልብስ)፣ የእጅ መስቀልና ሻሽ ተበርክቶላቸዋል።

የደብረ ምጥማቅ ቅዱስ ፊልጶስ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፸፰ ዓ.ም ለሰባት አጥቢያዎች የመቃብር አገልግሎት እንዲሰጥ ሲወሰን ሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ገዳም የሰባቱ አጥቢያዎች ገበዝ በመሆን አገልግለዋል። አድባራትን በአገልግሎት እና ንዋየ ቅድሳት በማሟላት ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ ከቃለ ዓዋዲ ውጪ በሆነ መንገድ አገልግሎታቸውን ሲፈጽሙ ከነበሩ አብያተ ክርቲያናት ጋር ከፍተኛ ትግል ያደርጉ የነበሩ እውነተኛ አገልጋይ አባት ነበሩ። ቤተ ክርስቲያን ከቃለ ዓዋዲ ውጪ በሆነ መንንገድ መተዳደር የለባትም ማለታቸውን አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አካላት ጉዳዩን የፖለቲካ ትርጉም ሰጥተውት አገልግሎታቸውን ሲያስተጓጉልባቸው እንደነበረም ይነገራል።

# በመላው ዓለም ያሉ ኦርቶዶክሳውያን ለአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘብ መቆም አለባቸው

*ክፍል አንድ*

*በካሣሁን ለምለሙ*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ፈተናዎች ያለፈችና እያለፈች ያለች ናት፡፡ ይህ መከራ ከዘመን ዘመን አይነቱና መጠኑ ይለያይ እንጂ አብያተ ክርስቲያናትን ለውድመት ምእመናንን ደግሞ ለመከራ ሲዳርግ ቆይቷዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ስደት የጀመረው አይሁዶች ጌታችንና መድኃኔታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ካሳደዱበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከዘመነ ድዮቅልጥያኖስ አስከፊ የቤተ ክርስቲያን ስደት በኋላ በሀገራችን ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን እናጠፋለን ብለው በተነሡ ዋና ዋና የቤተ ክርስቲያናችን ጠላቶች ማለትም ዮዲት ጉዲትና አሕመድ ግራኝ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ታሪክ የማይረሳው የከፋ ጥፋት ፈጽመዋል፡፡ እነዚህ የጥፋት ኃይሎች በዘመኑ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋ ቢነሡም ቤተ ክርስቲያን ግን በክርስቶስ ደም የተመሠረተችና ጸንታ የቆመች በመሆኑ እንኳን ሊያጠፏት ከሙላቷ አላጎደሏትም፡፡

በእኛ ዘመንም ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን በተለያየ ሁኔታና ቦታ ለጥቃትና ለስደት ተጋላጭ ሆነው እያስተዋልን እንገኛለን፡፡ ከዚህ ቀደም የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ካደረሱት እልቂት በላይ ካለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ የደረሰውና እየደረሰ ያለው ጥፋት የከፋ መሆኑን ማንም ሰው መታዘብ ይችላል፡፡ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ማለትም በኦሮሚያ፣በደቡብ፣በአማራ፣ በሶማሌ፣ በአዲስ አበባ፣በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በሲዳማ ክልሎችና በሌሎች አካባቢዎች በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ አክራሪዎች ከፍተኛ ጥቃት የፈጸሙ ሲሆን ዛሬም ይህ እኩይ ድርጊት ሳይቆም ሰሞኑን በደቡብ ክልል በስልጤ ዞን ሥር ባሉ ወረዳዎችና ቀበሌዎች አክራሪ እስላሞች በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል፡፡

በጥቃቱም አራት አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፤ አሥራ ሁለት ምእመናን በግፍ ሰማዕትነትን ተቀብለዋል፤ ሠላሳ አንድ ምእመናን እንዲሁ ለቀላልና ለከባድ የአካል ጉዳት ተዳርገዋል፤ሌሎች ምእመናንም ለከፍተኛ የሥነ ልቡና ቀውስ ተዳረገዋል፤ ከልጅነት እስከ ዕውቀት ያፈሩት ሀብት ንብረታቸውም በአንድ ጀንበር ወድሟል፡፡ እስካሁን ድረስ ያለምንም ጥፋታቸው በእስር የሚማቅቁና የሥነ ልቡና ጉዳት (ስድብና ማስፈራሪያ) እየደረሰባቸው ያሉ ምእመናን መኖራቸውን ሀገረ ስብከቱ አስታውቋል፡፡ ዝግጅት ክፍላችንም በስልጤ ዞን አክራሪ እስላሞች በፈጸሙት ጥቃት የደረሰውን ጉዳትና እየተወሰደ ስላለው ዘላቂ መፍትሔ እንዲነግሩን የሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ ደስታን እንግዳ አድርገን ጋብዘናቸዋል፡፡ ከእርሳቸው ጋር የነበረንን የስልክ ቆይታ በሚከተለው መልኩ አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡



ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ ደስታ (የሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ)

**ስምዐ ጽድቅ፡- በቅርቡ በስልጤ ዞን የተፈጸመውን ሃይማኖት ተኮር ጥቃት አስመልክቶ ባደረጋችሁት የመጀመሪያ ዙር ቅኝት ምን ተመለከታችሁ?**

**ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ ደስታ፡-** በቅርቡ በሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ስልጤ ዞን የሃይማኖት አክራሪዎች በፈጸሙት ሃይማኖት ተኮር ጥቃት የደረሰውን ውድመት ለማጥናት በዞኑ የተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ትላንት ማለትም ግንቦት ፪ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም ላይ ቅኝት አድርገናል፡፡ ቅኝታችንን ለማድረግ ያሰብነው ጥቃቱ

ከተፈጸመበት ማግስት ጀምሮ ቢሆንም የክልሉና የዞኑ የመንግሥት አመራሮች በተለያየ ምክንያት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ችግሩ ከደረሰ ከሁለት ሳምንት በኋላ ሄደን የዳሰሳ ጥናት አካሄደናል፡፡ በቅኝቱ ወቅት የደቡብ ብሔር ብሔርሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ተወካዮች፣ የስልጤ ዞን አመራሮች፣የሀገረ ስብከቱ የሥራ ኃላፊዎች፣በማኅበረ ቅዱሳን የሆሳዕና ማእከል አገልጋዮች፣የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ኅብረት ተወካዮች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸውና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል፡፡

ቅኝቱ የተጀመርው በዞኑ ከሚገኘው ወራቤ ከተማ ሲሆን በከተማው የሚኖሩ ምእመናን የከፋ ሞት፣የአካል ጉዳት፣የሥነ ልቡና ስብራት የሀብትና የንብረት ውድመት ደርሶባቸው ተመልክተናል፡፡ ቤታቸው የወደመባቸውና የሚለብሱት የሚጎርሱት ያጡ በርካቶች እንደሆኑ ታዝበናል፡፡

ጥቃቱን ሸሽተው ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተሰደዱ ምእመናን፣ካህናትና አገልጋዩች እንደነበሩም ከቅኝቱ ተረድተናል፡፡ ከሞትና ከአካል ጉዳት በእርሱ ቸርነት የተረፉ ምእመናን በየዕለቱ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑበት ሕንጻ ቤተ መቅደሳቸው በአክራሪዎች በመውደሙና እግዚአብሔርን በጸሎት የሚጠይቁበት ቦታ ለጊዜው ባለመኖሩ ተቸግረው አይተናል፡፡ አምልኮተ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ትንሽ መቃኞ ቤት እንዲሠራላቸው እኛን ሲማጸኑ ነበር፡፡

በዚያ ሁሉ የመከራ ጊዜ እንደቀደሙ አባቶቻቸው መልካም ሥራ ሠርተው የጠበቁን ካህናት አገልጋይ አባቶች መኖራቸውን ተመልክቻለሁ፡፡ አክራሪዎች የወራቤ ቅዱስ ሩፋኤል ሕንጻ ቤተ መቅደስን ሊያቃጥሉና ሊያወድሙ ሲመጡ የራሳቸው ሀብትና ንብረት እየተቃጠለ ታቦተ ሕጉን ጨምሮ የከበሩ ንዋያተ ቅድሳት የጥፋት ኃይሎቹ በማይደርሱበት ቦታ ደብቀው በማስቀመጥና ከፍተኛ ዋጋ በመክፍል ከጥፋት ታድገዋል፡፡ የእነዚህ አገልጋይ አባቶች መልካም ተግባር ዛሬም ድረስ ለቤተ ክርስቲያን ክብር ሲሉ ዋጋ መክፍል የሚችሉ እልፍ አባቶች እንዳሉ ሕያው መስክር ሆኗል፡፡ በዚህ ዘመን ያለው ትውልድም ከእነዚህ አባቶች ሃይማኖታዊ ተጋድሎ በመማር ቤተ ክርስቲያኑንና ቅርሱን እንዲጠብቅ አባታዊ መልእክት አስተላልፋለሁ፡፡

እነዚያን የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ከጥፋት የታደጉ አባቶች የራሳችው ሀብትና ንብረት ወድሞባቸው ዛሬ በስደትና በሥቃይ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ይህ ለአንዲት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተከፈለ ትልቅ ዋጋ ነው፡፡ በስልጤ ዞን ለቤተ ክርስቲያን ሲሉ ዋጋ የከፈሉ አገልጋይ አባቶችንና ምእመናንን ማጽናናት፣የተሰደዱትንም ወደ አካባቢያቸው መመለስ፣የወደመውን መተካት እንዲሁም የደኅንነት ዋስትና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ተግባር በቀጣይ ከዞኑና ከክልሉ የመንግሥት አመራሮች ጋር በጋራ በመሆን ትኩረት ሰጥተን የምንሠራ ይሆናል፡፡

የሁለተኛው ቅኝት መዳረሻ የሆነችው ደግሞ የቂልጡ ፍኖተ ሎዛ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ በአማረ መልኩ ከታነጸች በጣም ቅርብ ጊዜ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያኗን በአክራሪዎች ቃጠሎ እንዳልደረሰባት የስልጤ ዞን የመንግሥት አመራሮች ሊያስረዱንና ወንጀሉን ለመሸፈን ቢሞክሩም አካባቢው ድረስ ሄደን ማጣራት እንደምንፈለግ ነግረናቸው ወደ አካባቢው ባመራንበት ጊዜ ሕንጻ ቤተ መቅደሱ አልወደቀም እንጂ በውስጡ የነበሩት ንዋያተ ቅድሳት ሙሉ በሙሉ ወድመውና ምድር ቤቱን ጨምሮ የሕንጻው የውስጥ ክፍል በእሳት ክፉኛ ተጎድቶ ተመልክተናል፡፡

እውነታውን ለመሸፈን ቢሞከርም በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰው ጉዳት በግልጽ ጎልቶ የታየ ሆኗል፡፡ በወቅቱ የዞኑ አመራሮች "ነገሩን የሚያባብስ ሳትሆኑ የእርቅና የሰላም ሰዎች መሆን አለባችሁ" ብለውናል፤እኛ ደግሞ እርቅና ሰላም የሚመጣው የተፈጸሙ ወንጀሎችን በመደበቅ ሳይሆን በግልጽ አውጥቶ ወንጀለኛው ተገቢውን ቅጣት ሲያገኝ ነው እንላለን፡፡ አክራሪዎችንና ወንጀለኞችን እየደበቁ ስለሰላምና እርቅ ማውራት የማይታሰብ ነው፡፡

በሦስተኛ ደርጃ የቅኝታችን መዳረሻ ያደረግነው የሳንኩራ ገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ሲሆን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ፣የካህናት ማደሪያው፣በጅምር ያለ አዳራሽና ሌሎች ንብረቶች ሙሉ በሙሉ በአክራሪዎች ወድሞ አግኝተናቸዋል፡፡ ከዚያም ሰንኩራ አቅራቢያ ዓለም ከተማ የሚገኘውን የቅዱስ ገብርኤል ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የተመለከትን ሲሆን ቤተ ክርስቲያኑ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ወድሟል፡፡ በዚህ ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ አባቶች ከዚህ ቀደም እንደጠቀስናቸው አባቶች ሁሉ ንዋያተ ቅድሳትን ደብቀው በማስቀመጥ ከአክራሪዎች ጥፋት ታድገዋል፡፡ ካደረግነው ቅኝት በኋላም ሁላችንም ወደ ጠቅላላ ውይይት ገብተናል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በምእመናን ሕይወትና አካል ላይ የደረሰውን ጉዳት በቅኝታችሁ እንዴት ተመለከታችሁት?**

**ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ፡-** በአካባቢው ካለው የፀጥታ ችግር አንጻር ይህ መጀመሪያ ዙር የዳሰሳ ቅኝት ነው፡፡ ቅኝት ጥናት ስላልሆነ በአሁኑ ሰዓት ሙሉ የሆነ በቁጥር የተደገፈ መረጃ ለማቅረብ ያስቸግራል። በቅኝታችንም ተደራሽ ያላደረግናቸው አካባቢዎች እንዳሉ እንረዳለን፡፡ ለአብነትም በወራቤ ዩኒቨርስቲ በኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ላይ የተፈጸመውን ጥቃትና የደረሰውን የጉዳት ዓይነትና መጠን ለማወቅ ተቋሙ የፌዴራል ተቋም መሆኑ ፈቃድ የሚገኘው ከፌዴራል መንግሥት ነው በሚል እንዳናጣራ ተከልክለናል፡፡ ይሁን እንጂ የተፈጸመውን ወንጀል ዩኒቨርስቲው ውስጥ ገብተን ለማጣራት ከፌዴራል መንግሥት ጋር ንግግር ጀምረናል፡፡

በቀጣይም ጉዳዩ የሃይማኖት እንጂ የፖለቲካ መልክ እንደሌለው ለመንግሥት አካላት በማስረዳት በእኛ የሃይማኖት አባቶች ብቻ እንዲታይ የምናደርግ ይሆናል፡፡ በዚህ ወቅት በቅኝታችን በወራቤ ዩኒቨርስቲ ጉዳት የደረሰባቸው ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች በሙሉ በተደረገላቸው ሕክምና ሁሉም በመልካም ጤንነት ላይ እንደሚገኙ ነግረውናል፡፡

ነገር ግን እኛ በአካል ተገኝተን አላጣራንም፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርስቲው ሁለት ተማሪዎች እንደሞቱና ከሰባ ዘጠኝ በላይ በወንጀል የተጠረጠሩ አክራሪዎች እንደታሰሩ ነግሮናል፡፡ ነገር ግን ይህ መረጃ ታማኝነት የሌለውና ወንጀልን ለመሸፈን ከሚደረግ ጥረት የዘለለ እንዳልሆነ ከዚህ በፊት ከነበረን ተሞክሩ መረዳት ችለናል፡፡ በዚህ ምክንያት ለጊዜው የተጎዱ ተማሪዎችን ቁጥር በእርግጠኝነት ለማወቅ ተቸግረናል፡፡

ከጥቃቱ ጋር ተያይዞ ስድስት ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎችን መታሰራቸውንም ነግረውን በአስቸኳይ እንዲፈቱ አሳስበናል፡፡ ችግሩ የሃይማኖት ጥቃት መሆኑ እየታወቀ የፖለቲካ መልክ በመስጠትና ኦርቶዶክሳውያንን አስሮ ማንገላታት መፍትሔ እንደማይሆንና ለማንም እንደማይጠቅም ለዩኒቨርስቲው አመራሮችና ለመንግሥት ተጠሪዎች ነግረናቸዋል። ችግሩ ጥልቅና ውስብስብ በመሆኑ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ በተገኙበት የመጨረሻ ጥናት እንደሚደረግና ውይይት እንደሚካሄድ ከወረዳ፣ ከዞን፣ከክልሉና ከፌዴራል የመንግሥት ኃላፊዎች ጋር መግባባት ላይ ደርሰናል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጥቃቱ ምክንያት የተሰደዱ ካህናትና ምእመናን ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱና ያሉትም እንዲጸናኑ ሀገረ ስብከቱ ምን ሥራ ለመሥራት አቅዷል?**

**ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ፡-** መጀመሪያ ጥቃቱ እንዲወገዝ፣የተጎዱ ምእመናን እንዲካሱ የወደሙ ንብረቶች እንዲተኩ፣የተፈናቀሉ ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱና የደኅንነት ዋስትና እንዲሰጣቸው የሚሉ ሐሳቦችን ለመንግሥት አካላት በቅኝቱ ወቅት አንሥተናል፡፡ በኦርቶዶክሳውያን ላይ ጥቃት የፈጸሙ አክራሪዎች ሁሉ በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ በአጽንኦት ጠይቀናል፡፡ ከላይ ያሉት የስልጤ ዞን አመራሮች በአንጻራዊነት የተሻለ ቢመስሉም ከታች ያሉት ኦርቶዶክሳውያን ጠሎች ከሆኑ ችግሩን የበለጠ ያባብሰዋል የሚል ስጋት እንዳለብን አስረድተናል፡፡

ሀገረ ስብከቱ ከዞኑ፣ከክልሉና ከፌዴራል የመንግሥት አካላት ጋር በመሆን የተፈናቀሉ ካህናትንና ምእመናንን ለመመለስ፣መደበኛ አገልግሎት ለመጀመር የወደሙ አብያተ ክርቲያናትንም በጊዜዊታነት በመቃኞ ለመተካትና ጊዜያዊ የካህናት ማረፊያ ለመሥራት ጥረት የምናደርግ ይሆናል፡፡ የተለመደው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳይቋረጥ የተሰደዱ ካህናትን ወደ አገልግሎት መመለስ የሀገረ ስብከቱ የመጀመሪያ ተግባር ይሆናል፡፡

የወደሙ አብያተ ክርስቲያናትንና የተቃጠሉ ንብረቶችን የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መልሶ ለመተካትና ለመገንባት ርብርብ እንደሚያደርግ በውይይታችን መሃል ነግረውናል፤ይሁን እንጂ የተሠራውንና የተተካውን ሀብትና ንብረት መልሶ የሚያወድም ሌላ አክራሪ ኃይል እንዳይነሳ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ለሙስሊሙ ማኅበረሰብም ሆነ ለመንግሥት አመራሮች አሳስበናል፡፡ አጠቃላይ በዞኑ የሞቱ ምእመናንና የወደመው ሀብት ንብረት በጥናት ተጣርቶ ከተረጋገጠ በኋላ መንግሥት፣ሙስሊሙ ማኅበረሰብና ኦርቶዶክሳውያን በጋራ በመሆን ለመተካት በውይይታችን ከስምምነት ላይ ደርሰናል። ስምምነቱ ሳይውል ሳያድር በቅርቡ ከግብ ይደርሳል የሚል ሙሉ እምነት አለኝ፡፡ ይህ ብቻ በቂ ባለመሆኑ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ክብርና መብት በዘላቂነት የማስጠበቅ ሥራ መሠራት እንዳለበት ለመንግሥት አመራሮችን በአጽዕኖት አስገንዝበናል፡፡

# ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ

እህተ ሚካኤል

*ልጆች! እንዴት ሰነበታችሁ! ሰላም እንደቆያችሁ ተስፋ እናደርጋለን እግዚአብሔር ይመስገን! ልጆች! ዛሬ የምንነጋራችሁ ስለ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ታሪክ ነው በጥሞና ተከታተሉን!*



ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ልጆች! ቅዱስ ዮሐንስ የተወለደው በ፫፻፵፯ዓ.ም (347 ዓ.ም) የክርስቲያኖች መናኸሪያ በሆነችው በአንጾኪያ ከተማ ነው፡፡ ወላጆቹም የስም አባቱ ሶኩንዲስ የእናቱ ስም ደግሞ አትናሲያ ይባላል፡፡ የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ወላጆች እጅግ ባለጸጋ ነበሩ፡፡ አባቱ የመንግሥት ባለሥልጣንና ከፍተኛ የመንግሥት ቦታ ላይ የነበረ ሰው ነው፡፡ እናቱ አትናስያ የሃያ ዓመት ወጣት እያለች ባሏ ሶኩንዲስ በመሞቱ የቅዱስ ዮሐንስን ታላቅ እኅትና ቅዱስ ዮሐንስን ብቻዋን የማሳደግ ኃላፊነት ወደቀባት፡፡ በዕድሜ ዘመኗም ሁለተኛ ባል ሳታገባ ልጆቿን ሃይማኖት በማስተማር በሥርዓት ያሳደገች ጽኑ ክርስቲያን ነበረች፡፡

ልጆች! ቅዱስ ዮሐንስ ሃያ ዓመት ወጣት እያለ ወደ አቴና(የዛሬዋ ግሪክ) በመሄድ በዘመኑ ገናና የነበረውን የግሪክ ፍልስፍናን ተማረ፡፡ ትምህርቱንም ሲጨርስ ወደ ትውልድ ሀገሩ ወደ አንጾኪያ በመመለስ በ፳፫ (23) ዓመቱ በ፫፻፸ ዓ.ም (370) ዓ.ም በሊቀ ጳጳሱ መላጢዮስ እጅ ተጠምቆ የሥላሴ ልጅነትን አገኘ፡፡ ከዚያም ወደ ገዳም በመግባት በምናኔ ለመኖር ወሰነ፡፡ ይህ ቅዱስ አባት ከተጠመቀበት ጊዜ ጀምሮ እጅግ አብዝቶ የሚጾም፣ ጸሎተኛ እና ከአንደበቱ ክፉ የማይወጣ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ በቅድስና የኖረ ሰው ነው፡፡

ልጆች! ቅዱስ ዮሐንስ ‹‹አፈ ወርቅ›› የሚለው ቅጽል ስም ከተሰጠው ምክንያቶች አንዱ ሲናገር፣ ሲያስተምር ንግግሩ ድንቅ ስለነበረ እንዲሁም ከአንደበቱ የሚወጣው ትምህርት እጅግ ጣፋጭ በመሆኑ ነው፡፡ ሌላው እና በግንቦት ፲፪ (12) በሚነበበው ስንክሳር ላይ እንደተጻፈው ከዕለታት አንድ ቀን ንጉሥ አርቃዲዮስ በእልፍኙ ተቀምጦ ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር ሲጨዋወት ሁሌም በአእምሮው ላይ የሚመላለስበትንና ጥያቄ ሆኖ የኖረውን ሓሳብ ይጠይቀዋል፡፡ ንጉሡ የጠየቀውም ሓሳብ ‹‹ በማቴ. ፩፥፳፭ ላይ ያለው እና የበኩር ልጇን እስክታወቀው ድረስ አላወቃትም›› የሚለው ምን ማለት እንደሆነና ‹‹ዮሴፍ አላወቃትም›› ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ይጠይቀዋል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም የንጉሡን ጥያቄ በደንብ በማብራራት የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ዘላለማዊ ድንግልና አስረድቶት ሲጨርስ በአዳራሹ ውስጥ የነበረች የእመቤታችን ሥዕል በሰው አንደበት ‹‹ሠናየ ተናገርከ አፈ ወርቅ፣ ዮሐንስ ልሳነ ወርቅ፣ ዮሐንስ አፈ በረከት›› ብላ ስትናገር ሁሉም በመስማታቸው ሰምተውም በማድነቅ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አፈ ወርቅ እንደተባለ ይነገራል፡፡

ልጆች! ቅዱስ ዮሐንስ በገዳማዊ ሕይወቱ የተመሰከረለት ለሌሎች አርአያ የሚሆን ጻድቅ፣ የወንጌል ሰባኪ፣ አስተማሪ እንዲሁም መካሪ ነበረ፡፡ ጳጳሱ መላጥዮስ በ፫፻፹፩ ዓ.ም(381 ዓ.ም) ዲቁና የሾመው ሲሆን በ፫፻፹፮ ዓ.ም (386 ዓ.ም) ደግሞ ጳጳሱ ፍላቭያን ቅስና ሹሞታል፡፡ በዚህ የቅስና ማዕረጉም ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በቅንነት፣ በታታሪነት ወንጌል በማስተማር ብዙዎችን ወደ ክርስትና በመመለስና የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲወርሱ በማስተማር ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሙሉ አቅሙ ይተጋ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ላይ ሳለም በ፫፻፺፭ ዓ.ም (በ395 ዓ.ም) የቁስጥንጥንያው(የዛሬዋ ኢስታምቡል) ሊቀ ጳጳስ ሲያርፍ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ተሾመ፡፡

ልጆች! ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በዘመነ ጵጵስናው ለቤተ ክርስቲያን ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎችን የሠራ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት ነው፡፡ በርካታ መንፈሳዊ መጻሕፍት ከመጻፉም በላይ በሚያስተምረው መንፈሳዊ ትምህርት እጅግ ተወዳጅ ነበረ፡፡ የተቀደሰ ሕይወቱ ብዙዎችን የሚማርክ ሁል ጊዜም እውነትን በመናገር በሀገሪቱ ውስጥ በተለይም በመንግሥቱ አካባቢ ይታዩ የነበሩ ብልሹ አሰራሮችን ፊት ለፊት በመቃወምና ሰዎቹንም በመገሰጽ ወደ ቀናው መስመር እንዲገቡ ይጥር ነበር፡፡

የቁስጥንጥንያው ንጉሥ አርቃዲዮስ ሚስት ንግሥት አውዶክስያ ገንዘብን እጅግ አድርጋ የምትወድ ሴት ስለነበረች የቅዱስ ዮሐንስን ተግሳጽና ምክር መስማት አትወድም ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ከቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ጋር አትስማማም ነበር፡፡ ንግሥቲቱ በዚሁ ገንዘብ ወዳድነቷ የተነሣ የአንዲት ደሃ ሴት መሬት ቀምታ ስለነበር እንድትመልስላት ቅዱስ ዮሐንስ ሲጠይቃት እምቢ በማለቷ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳትገባ፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እንዳትቀበል በአጠቃላይ ከማኅበረ ምእመናን እንድትለይ አወገዛት፡፡ በዚህ የተበሳጨችው ንግሥት አውዳክዮስ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በወታደሮች አሲዛ ከከተማ ካስወጣችው በኋላ ‹‹አጥራክያ››ወደምትባል ደሴት ተወስዶ እዲታሰር አደረገችው፡፡

ልጆች! አውዶክስያ በቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ላይ የፈጸመችውን ግፍ የሰሙት የሮም ንጉሥ አፍሬዎስ እና የሮም ጳጳስ ቅዱስ ናክኒደስ ወደ ንጉሡ አርቃዲል መልእክት በመላክ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅን ከግዞት ፈትተው ወደ መንበረ ጵጵስናው እንዲመልስ ጠየቁ፡፡ ንጉሡም ቅዱስ ዮሐንስ ከታሠረበት ደሴት ተፈቶ እንዲመጣ አድርጎ ወደ መንበረ ጵጵስናው መለሰው፡፡ ነገር ግን ቅዱስ ዮሐንስ ቀድሞ የነበረውን አቋም የማይቀይር በተለይም ለሥልጣን ብሎ በንግሥቲቱ የግፍ ሥራ የማይተባበር መሆኑን ስታውቅ መልሳ ወደዚያው እንዲታሰር ወደዚያው ደሴት በግዞት ላከችው፡፡ በደሴቲቱ ላይ የነበሩት ሰዎችም ጣዖት አምላኪዎች ነበሩና ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ወንጌልን በማስተማር አጥምቆ ካህናትንም ከመሀከላቸው ሾሞላቸዋል፡፡

በዚያው በግዞት እያለ በ፬፻፯ ዓ.ም(407 ዓ.ም) በ፷ ዓመቱ ግንቦት ፲፪ አረፈ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በሕዝቡ ዘንድ እጅግ ይወደድና ይከበር የነበረ አባት ስለ ነበር ገና በስድሳ ዓመቱ ማረፉ ለሕዝቡ እጅግ መራር ኀዘን ነበር፡፡ በቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ለተተካው የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ በቅዱስ ጵሮቅለስ እግር ሥር ወድቀው የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅን ቅዱስ አጽም ካረፈበት ደሴት እንዲያመጣ ለመኑት፡፡ እርሱም ወደ ንጉሡ ዘንድ በመሄድ እና በመለመን የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ አጽም እንዲመጣ አደረገ፡፡ የፅንቊ ፈርጦች ባሉት የእብነ በረድ ሳጥን ውስጥ አድርገውም በታላቅ ክብር ወደ ቊስጥንጥንያ አፍልሰው አመጡት፡፡ በሃጊያ ኤሬነ አሳረፉት፡፡ የዚህ ቅዱስ አባት ፍልሰተ አፅሙ የሚከበረው ኅዳር ፲፯(17) ቀን ነው፡፡

ልጆች! ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ለቤተ ክርስቲያን ታላላቅ ምስጢሮችን ያዘሉ መጻሕፍትን ጽፎ ያበረከተና በግንቦት ፲፪ ቀን ያረፈ ቅዱስ አባት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያንም እርሱ የደረሳቸውን መጻሕፍቶችን ለተለያዩ አገልግሎቶች ስትጠቀምባቸው ትኖራለች፡፡ እኛም ይህ ቅዱስ አባት ካደረጋቸው ተአምራት አንዱን ነግረናችሁ እናብቃ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ አንድ ቀን አንዲት ሕፃን ልጅን ክርስትና ሊያነሳ ሲሄድ መልአከ ሞት ደግሞ ሕፃኗን ሊቀስፍ ሲሄድ በመንገድ ላይ ተገናኙና ዮሐንስ ‹‹ወዴት ትሄዳለህ?›› አለው፡፡ መልአከ ሞቱም ‹‹ሕፃኗን በሞት ቅሰፍ ተብዬ ተልኬ ልቀስፍ እየሄድኩ ነው›› አለው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም ‹‹ሳትጠመቅና ልጅነትን ሳታገኝ እንዳትቀስፋት እስካጠምቃትም ድረስ እንዳትንቀሳቀስ›› ብሎ በሥልጣነ ክህነቱ አስሮት ሄደና ሕፃኗን ካጠመቃት በኋላ አረስቶት በሌላ መንገድ ተመለሰ፡፡

መልአከ ሞቱም በዮሐንስ ሥልጣነ ክህነት ታስሮ ፲ ዓመት እንደቆመ ቆይቷል፡፡ ከ፲ ዓመት በኋላ ዮሐንስ በዚያ መንገድ ሲያልፍ መልአከ ሞትን ቆሞ ሲያየው ‹‹ለምን ጉዳይ ቆመሃል?›› አለው፡፡ መልአከ ሞትም ‹‹የዛሬ ፲ዓመት አንተ ስትሄድ እንዳትንቀሳቀስ ስላልከኝ ሥልጣንህ እንደሰንሰለት አስሮ ይዞኛል›› ቢለው ዮሐንስም ይህን ያህል ጊዜ በመርሳቱ ተጸጽቶ ‹‹ተሳስቻለሁ በል ሂድ ግብርህን ፈጽም›› ብሎት መልአከ ሞትም ሄደና ልጅቱን ቀስፎ ዐርጓል፡፡ ዮሐንስም እቦታው ሲደርስ ቤተሰቦቿ ሲያለቅሱ ቢያገኛቸው አጽናንቷቸው ተመልሷል፡፡

ልጆች! የቅዱስ ዮሐነስ አፈ ወርቅን ሕይወት ከውልደቱ እስከ እረፍቱ እንዲሁም ለምን ‹‹አፈ ወርቅ›› እንደተባለ በመጠኑም ቢሆን እውቀት አግኝታችኋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በሚቀጥለው ጊዜ ደግሞ በሌላ ታሪክ እስከምንገናኝ ሰላም ሁኑ፡፡

እኛንም በዚህ ቅዱስ ጸሎት ይማረን! በረከቱ ከእኛ ጋር ትኑር አሜን!

**ምንጭ** -- ስንክሳር ግንቦት ፲፪

--- ዲ.ን ያረጋል አበጋዝ፤ ‹‹ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ››፤ 2ኛ እትም፤ ግንቦት ፳፻፫ ዓ.ም

--- ድርሳነ ቅዱስ ዮሐንስ

# መረሳት የሌለበት የካህናት ሚና

**ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በረጅም ጊዜ ታሪኳ ውስጥ ታላቅ፣ ብርቱና የተደነቀ የካህናት የአገልግሎት ታሪክ ያላት ቤተክርስቲያን ነች፡፡ ካህናት በማህበረሰብ ውስጥ ያላቸው ክብርም ከፍ ያለና ዘርፍ ብዙ ሚና እንዲጫወቱ ዕድል የሚሰጣቸው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ካህናት የኢትዮጵያውያን ማኅበራዊ ግንኙነት በኦርቶዶክሳዊ እምነት ባህል እንዲቃኝ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ራሳቸው ካህናቱ በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ የመሪነት፣ የአነቃቂነት፣ የአበረታችነት ሚና ነበራቸው፡፡ በሚያስደስቱም በሚያሳዝኑም የማኅበራዊ ሁነቶች ውስጥ ጎልተው ይታያሉ፡፡ ተከባሪ፣ ተደማጭ ነበሩ፡፡ ይህ ተጽእኖ ከማኅበራዊ ኑሮ ተሻግሮ ፖለቲካዊ ጥላም ነበረው፡፡

አሁን፣ አሁን ግን ውጪዊ ግፊቶች እንዳሉ ሆነው ካህናት በየዘረፉ ብዙ የማህበረሰቡ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሳያፍሩ፣ ሳይፈሩ የሚያደርጉት ተሳትፎ እየቀነሰ አገልግሎታቸው በአጥቢያቸው በሚሰጥ መንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ እየተገደበ መምጣቱን እናስተውላለን፡፡ የህ ደግሞ ካህናቱ እየተገፉ ጫና እያረፈባቸው ብቻ አይደለም ለትዝብት የሚያዳርገው አብዛኞቹ ካህናት በራሳቸውም ምክንት ሲያፈገፍጉ ማስተዋሉ ነው፡፡

ሰው ክፉም ይሁን ደግ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ አይለይም ካህንም እንዲሁ አገልግሎት የሚሰጠው ማህበረሰብ ባለበት አካበቢ ከሚኖር ሰው ሁሉ ጋር ሰላም፣ ፍቅር፣ ትብብር፣ በጎነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ማህብረሰቡ በጥቅል ችግር ሲገጥመው ጥበብን፣ ምክርን በማካፈል፣ መውጫ መንገድ በማመላከት ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህ የመጋቢነትም ሚና ነው፡፡ ይህ ሚና ግን ዛሬ ላይ ምን ያህል አለ የሚለው ጥያቄ የሚነሣበት ሆኗል፡፡

ካህናት ሰዎችን ለማገልግል ቃልኪዳን የተቀበሉባቸውን ምእመናን ያለአድልዎ ለማገልገል ያላቸው መንፈሳዊ ሕይወት ቁርጠኝነት ምን ያህል ነው የሚለው አሳሳቢ ሆኗል፡፡ አንዳንድ ካህናት በአደባባይ በቋንቋ ለይቶ ሰዎችን ለመቅረብ፣ በሀብት ደረጃ ወይም በድህነትና በሀብታምነት ላሉ ሰዎች የሚሰጡት ቀረቤታ ጥያቄ የሚነሣበት እየሆነ ነው፡፡ ጥቂት እርሾ ብዙውን ሊጥ እንዲለውጥ እንዲህ ይህ የፈሪሳውያን የሚባለው እርሾ በአንዳንድ የዘመናችን ካህናትም ውስጥ እንዳይስፋፋ ያሰጋል፡፡ ካህናት ድሆችን በፍጹም ርህራሄ እንዲያገለግሉ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህ ከሐዋርያት ጀምሮ ሲደረግ የነበረ ነው፡፡ ሐዋርያት ምንም አልነበራቸውም፤ ነገር ግን በዘመናቸው የነበሩ ምእመናንን እያስተባበሩ ድሆችን ይድግፉ ያጽናኑም ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ‹‹ድሆችን እናስብ ዘንድ ብቻ ለመኑን ፥ ይህንም ደግሞ ላደርግ ተጋሁ፡፡›› (ገላ ፪፥፲) ብሏል፡፡

በዚህ ዘመን ድሆች በሚደገፉበት መንገድ ድጋፍ እንዲያገኙ መደረግ ያለባቸውን ነገሮች ሁሉ ለማድረግ ካህናት ቅድሚያውን ሊወስዱ ይገባል፡፡ በቅርቡ በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ በጦርነት ለተፈናቀሉና ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች የተደረገው ድጋፍና እንክብካቤ እንደአርአያ እንዲታይ ያደረገው ተግባሩ የቤተ ክርስቲያን ሆኖ የኖረ፣ ወደፊትም መኖር የሚገባው ሆኖ ሳለ ከነገሩ ምን ያህል መራራቅ እንደተፈጠረ አመላካች ነው፡፡ አብዛኞቹ የድጋፍና የርኅራኄ ሥራዎች በአንዳንድ ምእመናን ጥረት ሲከናወኑ እናያለን እንጂ የካህናቱ ተነሣሽነት፣ ምክርና፣ መሪነት በሚፈለገው ደረጃ የሚታየበት አለመሆኑ ግን እያስተዛዘበ ነው፡፡ ካህናት ከራሳቸው ጀምሮ ምእመናንን በማስተባባር ድሆች የሚደገፉባቸውን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማቋቋም ወይም ምእመናናን እንዲያቋቁሙ የማስተማር የማነሣሣት ሥራ ላይ መዘግየት አይገባቸውም ነበር፡፡

ካህናት ሁሉን እንደ አቅሙ፣ እንደማንነቱ፣ እንደ አኗኗሩ እየቀረቡ በሰላም፣በፍቅርና በእርጋታ ለማስተባበርና ለማረጋጋት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያንም ሁሉን እንደ ሁኔታው እንዲቀርቡ

‹‹ሽማግሌ የሆነውን አትገሥጸው፥ እርሱን ግን እንደ አባት፥ ጎበዞችን እንደ ወንድሞች፥ የሸመገሉትን ሴቶች እንደ እናቶች፥ ቆነጃጅቱን እንደ እኅቶች በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው። በእውነት ባልቴቶች የሆኑትን ባልቴቶች አክብር።….›› (፩ኛ ጢሞ. ፭፥ ፩-፪) ተብሎ እንደታዘዘው ሁሉ በምድር የሚኖሩ የትኞቹንም ሰዎች ደግሞ በማህብራዊ ግንኙነቱ ምክንያት የሚቀርቡበት መላ ሊኖራቸው ግድ ነው።

ካህናት ከድሆች ጋር ብቻ ሳይሆን ከሀብታሞችም ጋር ቅርበት ቢኖራቸው አያስነቅፍም፤ ይህ ግን ለራሳቸው ኑሮ የሚያደላድሉበት ቀረቤታ ሳይሆን ሀብታሞችን በማስተባበር በገንዘባቸው መልካሙን እንዲያደርጉ፣ በሀብታቸው በከፈቷቸው ድርጅቶች የሚያሠሯቸውን ሠራተኞች በቅንነትና በፍትሐዊነት እንዲያስተዳድሩ፣ ሀብታቸውን ለበጎ አድራጎት ሥራ እንዲያካፍሉ የሚመክሩበት ቀረቤታ ሊሆን ይገባል እንጂ። ዛሬ ዛሬ ግን ከካህናቱ ይልቅ የመናፍቃን አፈቀላጤዎች ተጽእኖ የሚያሳድሩባቸው ባለሀብቶች እየበዙ ነው።

ካህናት ኑሮ የተደላደለላቸውን፣ ቤታቸው የሞቀላቸውን ወላጆቻቸው የቆሙላቸውን ልጆች ብቻ ሳይሆን አሳዳጊ ለሌላቸው ልጆችም በቅርበት መገኘት አለባቸው። የሙታን ልጆች ለማደግ የሚሔዱባቸውን ተቋማትም ሊፈጥሩ የሚገባቸው ካህናት ናቸው። አሁን ግን ምን ያህሉ የሙታን ልጆች በካህናት አስተባባሪነት በተቋቋሙ ተቋማት ውስጥ ያድጋሉ ብለን ብንጠየቅ የካህናቱ ሚና ዝቅ እያለ መምጣቱን ብዙ ሳይመረምሩ ለመረዳት ይቻላል።

ካህናት ሕፃናትን ብቻ ሳይሆን ጧሪ የሌላቸውን አረጋውያንም እንዲደገፉ ሊጸልዩላቸውም፣ ምእመናንንም ሊያሳስቡላቸው፣ የመጦሪያ ተቋማት ሊፈጥሩላቸውና ሊያስፋፉላቸውም ይገባል። በአጥቢያው ያሉ ማህበረ ካህናት በየአካባቢያቸው ባሉ የሕክምና ማእከላት ተገኝተው የታመሙትን ለመጎብኘት ብርታትና ንቃት ሊኖራቸው ይገባል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ የታመሙ ወገኖችን ሲፈውስ፣ ሲያጽናና ኖሯል። ካህናትም አለቃቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን በማድረግ ሊመስሉት ይገባል። ግን አሁን የካህናት ሚና በዚህ ረገድ ምን ያህል አመርቂና ተጽእኖ ፈጣሪ ነው? ምን ያህሎቻችን በሆስፒታል በካህናቱ ተጎብኝተናል? ማጽናኛ ቃልስ ሰምተናል? ምን ያህሉን ሆስፒታሎች ካህናቱ በምን ያህል ጊዜ በጋራና በተናጠል ይጎበኙአቸዋል? የሚለው ብዙ ጊዜ በትዝብት የሚታይ እየሆነ ነው።

እንዲሁም ካህናት ከታመሙት ጋር ብቻም ሳይሆን ምዕመናን በማረሚያ ቤት በፍትሕ መቅናት ወይም መጣመም ምክንያት ሊገኙ ይችላሉና ታርመው እንዲፈቱ ለንስሓም እንዲበቁ መምክር የካህናት ሥራ ነው። በግፍ የታሰሩም እግዚአብሔር ከመከራ እንዲያወጣቸው መጸለይና ሄዶም ማጽናናት ያስፈልጋል። ይህ ሁሉ ደግሞ በጌታ ቃል እንዲፈጸም የታዘዘ የኃጢአት መደምሰሻ፣ ለመንግሥተ ሰማያት መውረሻ በመሆኑ በወንጌል ‹‹ እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና።›› (ማቴ ፳፭፥፴፬) ተብሏል።

ይህ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ካህናት የሚጠበቅ የማኅበራዊ ሕይወታቸው መገለጫ ነው። ካህናት እንደማንኛውም ዜጋ በሚኖሩበት ሀገርና ማህብረሰብ ይኖራሉ። በዚህ የኑሮ ዐውድ ውስጥ ደግሞ ሊመለሳሱ የሚገባው ከክርስቲናዊ ሕይወታቸው በተቀዳ የማህበራዊ ግንኙነት መገለጫዎች ነው። እነዚህ የግንኙነት መገለጫዎች ማንንም የማይጎዱ የካህኑንም ክብርና መንፈሳዊ ሕይወት የማይጎዱ ናቸው። እግዚአብሔር ለክፉውም ለደጉም ፀሐዩን እንደሚያወጣ ዝናቡንም እንደሚያዘንብ በማኅበራዊ ግንኙነቶች ውስጥም ካህናት አባታቸውን አምላካቸውን መምሰል ይጠበቅባቸዋል። በዘመናችን እየተንደለ የመጣውን ይህንን የካህናት ሚና በፍጥነት እውን ማድረግ ወይም ብልጭብልጭ የሚለውን አጉልቶ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል እንላለን።

# ስርቆት ይሆንብኝ ይሆን?

ውድ የስምዐ ጽድቅ አዘጋጆች እንዴት ከረማችሁ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ዕረፍት ለሚነሳኝ ነገር የመፍትሔ ምክር ትለግሡኝ ዘንድ ልጽፍላችሁ ብዕሬን አነሣሁ ጉዳዩም ይህ ነው፡፡ እኔ የመንግሥት ሠራተኛ ነኝ፤ በኃላፊነትም እየሠራሁ እገኛለሁ፡፡ ብዙ ጊዜዬንም በመስክ ሥራ አሳልፋለሁ፡፡ ከዚያ ጋር ተያይዞ መሥሪያ ቤቴ የሚከፍለኝ የአበል ክፍያ ሲሆን ዘወትር የምፈተንበት ጉዳይ እየሆነ ነው፡፡ ምን መሰላችሁ? የሚከፈለኝ አበል አንድ ሺህ አምስት መቶ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ሺህ ብሩ ለአልጋ በደረሰኝ የሚወራረድ ተብሎ ይሰጠኛል፡፡ ይህ ግን ብዙ ጊዜ ምቾት ስለማይሰጠኝ ዝቅተኛ ዋጋ ባላቸው አልጋ ቤቶች እያደርኩ የማወራርደውን ደረሰኝ ግን በሕገ ወጥ መንገድ ሰብስቤ ለማወራረድ እሞክራለሁ፡፡ ሁኖም በሚተርፈኝ ገንዘብ ደስ ቢለኝም ገንዘቡን ለማትረፍ የሔድኩበት መንገድ ደግሞ የአእምሮ ዕረፍት ይነሣኛል፡፡ ይህ ነገር ምን አልባት ስርቆት ይሆንብኝ ይሆን? ምክራችሁን በጥበቅ እሻለሁ፡፡››

ውድ ጠያቂያችን! በዚህ ዓለም ሰንኖር ለእግዚአብሔር ሕግ እንገዛለን፤ እንዲሁ ደግሞ በዓለም ውስጥ ያሉ የገዢዎችን ሕግጋትም እናከብራለን፡፡ የመንግሥት ሕግ የተከበረ ነውና፡፡ በዐላውያን መንግሥታት ፊት ለሰማዕትነት የምንቆምበት ጊዜ ደግሞ አለ፡፡ ይህም ዐመፅ ሳይሆን የሕይወታችን ቀይ መስመር ሆኖ በእምነት ሕይወታችን ተጻርሮ የሚመጣ አዋጅ ካለ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ እንቃወማለን፤ ለኃጢአት ሕግም አንገዛም እንላለን፡፡ እግዚአብሔር በረዳን ልክም ሰማዕትነትን እንቀበላለን፡፡

ከዚህ ውጪ ግን ለመንግሥታት /ለገዢዎች/ እንድንታዘዝ የአባቶቻችን ሐዋርያት ትምህርት አለን፡፡ ‹‹ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፤ ለንጉሥም ቢሆን፥ ከሁሉ በላይ ነውና፤ ለመኳንንትም ቢሆን፥ ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት በጎም የሚያደርጉትን ለማመስገን ከእርሱ ተልከዋልና ተገዙ፡፡ (፩ኛ ጴጥ. ፪፥፲፫) ተብለናል፡፡ ለመንግሥታት /ገዢዎች/የመገዛታችን ማሳያ በዚህ ዓለም እንድንኖርበት ያወጡትን ሥርዐት/ ሕግ፣ መመሪያ ፣ ደንብ፣ አዋጅ በማክበር፣ በማስከበር ነው፡፡

ውድ ጠያቂያችን! እርስዎ ያነሡት የአበል አከፋፈልና አጠቃቀም የመሥሪያ ቤትዎ መመሪያ የመንግሥትዎ ሕግ አካል ነው፡፡ የሚያስጨንቅ ቢሆንም በጊዜው ጊዜ የሚመች ሆኖ እስከሚዘጋጅ ሕግ ነውና የማክብር ግዴታ አለብዎት፡፡ በእርስዎ ሐሳብ ነገሩ ‹‹ከስርቆት ይቆጠርብኝ ይሆን?›› እንዳሉት በዚያ መልክ የመታየት ዕድል እንዳለው የሚያመለክተው የመጀመሪያው የኅሊና ክስዎ ነው፡፡ ነገሩ ለራስዎ ኅሊና አልመች ያልዎት የሚያስጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡ ከሕግ ከመመሪያ ማፈንገጥዎን ኅሊናዎ እየነገርዎ ነው፡፡ ‹‹ስለ ቍጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው፡፡›› (ሮሜ ፲፫፥፭) ከዚያም በላይ ግን ስርቆት ከአንድ ሰው ኪስ ገንዘብን፣ ከአንድ ሰው ቤት ንብረትን በስውር የመውሰድ፣ ወስዶም የመጠቀም ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ለስርቆት ብዙ መልክ አለው፡፡

ከብዙውም አስቀድሞ እግዚአብሔር ‹‹አትስረቅ፡፡›› (ዘፀ. ፳፥፲፭) ብሎ በሰጠው ሕግ ውስጥ ብዙ ዓይነት ካለው ስርቆት ሁሉ እንድንቆጠብ ገዢ ቃል ሆኖ የተሰጠ ነው፡፡ በሌላው በኩል በጥንት ጊዜ በነበረው ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በየዘመኑ የሚመጣ ትውልድ ከሚያካሒደው አኗኗር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ብዙ ዓይነት ስርቆት ይኖራል፡፡

ስርቆት ሲባል በኃይል፣ በተንኮል የሌላ ሰው የሆነን ነገር የራስ የማድረግ ነገር ነው፡፡ የስርቆት ሐሳብ ያላቸው ሰዎች ደግሞ ይሄንን በተለያየ መንገድ ሲፈጽሙት ይታያል፡፡ በዚህ ዘመን ደግሞ እርስዎ ከገጠመዎ አበልና ተመሳሳይ ነገሮች ጋር በተያያዘ ሰዎች በየራሳቸው አሳማኝ ወይም የማያሳምን ምክንያት ላይ ተደግፈው ሕጉ ከሚፈቅድላቸው (ከሚያዝላቸው) ውጭ ለመጠቀም ይሞክራሉ፡፡ ይህ ግን ለኅሊና ዕረፍት የማይሰጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም ሕግም የሚያስጠይቅና ቅጣትን የሚያመጣ ነው፡፡ መጽሐፍም ‹‹ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ›› ማለቱን መርሳት አይገባንም፡፡ (ሉቃ ፫፥፲፫)፡፡

ታዲያ ከእነዚህ ብቻ ሳይሆን ከብዙ እንደ ስርቆት ሊታዩብን ከሚችሉ ነገሮች ሁሉ መቆጠብ ያስፈልጋል ለምሳሌም ሰውን አደራ ተቀብለው የሚክዱ ሰዎች እንደ ስርቆት/ኃጢአት ተቆጥሮባቸው እንደነበር ከመጽሐፍ ቃል እንረዳለን፡፡ ‹‹ያኖረበትን አደራ ወይም ብድር ወስዶ ባልንጀራውን ቢክድ፥ ወይም ቢቀማ በሙሉ ይመልስ፥…›› (ሌዋ ፮፥ ፪) እንዲል፡፡

ሰዎች እንኳን ሆን ብለው ሠርተውት ቀርቶ የነገሩ ባለቤት

በቸልታ፣ በዝንጋዔ ወይም ሳያውቅ በመጣል ያጣውን ንብረት፣ ገንዘብ፣ የፈጠራ ሐሳብ.... ሌላ ሰው አግኝቶ ሳያሳውቅ ያለእርሱ ፈቃድ ሲጠቀም መገኘት ስርቆት / ኃጢአት ሊሆንበት እንደሚችል መጻሕፍት ያስረዳሉ፡፡ ‹‹የወንድምህ በሬ ወይም በግ ጠፍቶ ብታይ ቸል አትበል፤ ወደ ወንድምህ መልሰው፡፡ ወንድምህም በአቅራቢያህ ባይሆን ወይም ባታውቀው ይዘህ ወደ ቤትህ ትገባለህ፤ ወንድምህ እስኪሻው ድረስ በአንተ ዘንድ ይቀመጣል፥ ለእርሱም ትመልሰዋለህ፡፡ እንዲህም በአህያው ወይም በልብሱ ታደርጋለህ፤ እንዲህም በወንድምህ በጠፋበት ነገር ሁሉ ባገኘኸው ጊዜ ታደርጋለህ፤ ቸል ልትለው አይገባህም፡፡ የወንድምህ አህያ ወይም በሬው በመንገድ ወድቆ ብታይ ከእርሱ ጋር ሆነህ አነሣሣው እንጂ ቸል አትበለው፡፡ (ዘዳ. ፳፪፥፩) ተብሏል፡፡

ውድ ጠያቂያችን! እርስዎ የስርቆትን የትርጉምና ብያኔ ከጥንቱ ዘመን የስርቆት ተግባር ጋር ብቻ ማያያዝ አይጠበቅብዎትም፡፡ ነገሮች እየተወሳሰቡ መጥተዋል፡፡ ሰዎችም በምድራዊ ኑሮአቸው ከሚገጥማቸው ጭንቀት አንጻር በስርቆት መራቀቅን እንደ መላ ሲይዙት ይታያል፡፡ ነገር ግን ነገሮች ሁሉ ከባለቤቱ ፈቃድና እውቅና ውጪ ሲደረጉ ስርቆት መሆናቸው አይቀርም፡፡

የመንግሥት ሀብትና ንብረትም የሕዝብ /የወል ሀብት ተደርጎ ስለሚታመን በሀገሩ ሕግ ሁሉ የመንግሥት በሚል መጠሪያ የተያዘ ነው፡፡ ስለዚህ መሥሪያ ቤትዎ ባልፈቀደው፣ ባላዘዘልዎ መንገድ የአበል ክፍያን እየሸራረፉ በሕገ ወጥ መንገድ ለማትረፍ መጣር ለነፍስም ለሥጋም የሚበጅ አይሆንም፡፡ ቢያንስ የቅርብ ሥራ ኃላፊዎን እውቅናና ፈቃድ መጠየቅ ግድ ይልዎታል፡፡

ውድ ጠያቂያችን! ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በብዙ ፈተና ሰንሰለት ውስጥ የሚያልፍ ነው፡፡ ፈተናዎች ደግሞ በአብዛኛው የሚመነጩት ለሥጋዊ ኑሮአችን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በምናደርገው ጥረት ውስጥ ነው፡፡ ይህ ግን በማይገባ መንገድ ሲፈጸም መልሶ ለሥጋም ፈተና ይወልዳል፡፡ ሕገ ወጥ ሥራዎች በሕግ ተጠያቂነት ያመጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ መልሶ በገንዘብ፣ በእስራት መቀጣትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ የሰብእና የሞራል ስብራቱም ቀላል አይሆንም፡፡ ትልቅም ይሁን ትንሽ ከሚመስሉን ኃጢአት ሥራዎች መቆጠብ የሚጠቅመው ነፍስን ብቻ አይደለም፡፡ ለሥጋችንም ነው፡፡ ለቤተሰባችንም ነው፡፡ የእኛ ለምናላቸው ሰዎች ክብርና ሞገስ ነው፡፡ ስለዚህ ከጥቃቅን ስሕተቶች መጠበቅ አለብን፡፡ ብዙ ጊዜ ሊቃውንቱ ትናንሽ ለሚመስሉን ነገር ግን የተከበረ በመንፈስ የበለጸገ ማንነታችንን ሊያጠፉ ከሚችሉ ኃጢአቶች እንድንቆጠብ የሚመክሩበትን ቃል እንጥቀስልዎ ‹‹ወይናችን አብቦአልና የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮች፥ ጥቃቅኑን ቀበሮች አጥምዳችሁ ያዙልን፡፡›› ይላል (መኃ ፪፥፲፭)፡፡

እነዚህ ጥቃቅን የሚመስሉ አታላይ ፍላጎቶቻችን የሚመነጩት በአንድ በኩል ምኞት ከመፈለግ ነው፤እሱም ‹‹በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን?›› (ያዕቆ ፬፥1) እንዳለው ነው፡፡ ሁልጊዜ ግን ከምኞቶች ብቻ ሳይሆን ከባዱ ግፊት የሚመነጨው ከችግር፣ ከጭንቀትና ከራስ ወዳድነትም ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ ዓለም ኑሮ የሚያስፈልገንን በማጣታችን፣ ሲያጥረን፣ ሲቸግረን የምንገባበት የኃጢአት ሥራ ይኖራል፡፡ ይህ ሲሆን ታዲያ በእግዚአብሔር ፊት የሚያስደስት ሊሆን አይችልም፡፡ ሕይወታችንን ልንሰጥ ቃል በገባንለት ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ውስጥ ቸገረን ተብሎ ስርቆት እንዲገባ የሚፈቅድ ሥርዓት የለም፡፡

በተአምረ ማርያም ጦም ውሎ ጦም ያድር የነበረውን ሰው ሰይጣን ወርቅ አስመስሎ ያቀረበለትን ማታለያ ተቀብሎ አምላኩን መካዱ ከወቀሳ አላዳነውም፡፡ በድንግል ማርያም አማላጅነት ከሞት ቢተርፍም፡፡ እናታችን ግን ‹‹ሰው ቢቸግረው ይለምናል እንጂ አይክድም›› እንዳለቸው እንዲሁ ብንቸገር ሰዎች እንዲረዱን እናስቸግር ይሆናል እንጂ ሕይወታችንን ወደሚያሳጣ፣ ቤተሰባችንንም ወደሚያዋርድ የስርቆትና ክህደት ተግባር መግባት የለብንም፡፡

ስለዚህ ውድ ጠያቂያችን ያነሡልን የአበል ጉዳይም በእንቅስቃሴዎ ጊዜ ገንዘቡ ስላልበቃዎት ወይም አትርፈው ለመመለስ በሚያደርጉት ጥረት ምክንያት ወደ ፈተና ያስገባዎት ይመስለናል፡፡ ነገሩን በተቻለ መጠን ለኅሊና በሚመች መንገድ ሕጋዊነቱን ጠብቆ እንዲሠሩ መምከር ከእኛ ይጠበቃል፡፡ ይህ ምናልባትም የብዙዎች ችግር ሆኖ የተወሰኑት እግዚአብሔርን በሚያስደስት መንገድ በጭንቀት ውስጥም ሆነው ቢሆን ታግሰው በአሠራሩ እየተጓዙ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ እርስዎም በትዕግሥትዎ ነፍስዎትን ለመጠበቅ ጥረት ቢያደርጉ መልካም ነው እንላለን፡፡ በተከታታይ የኅሊና ክስ የሚያስጨንቅዎ ከሆነ ደግሞ ከመምህረ ንስሓዎ ጋር በመመካከር ዕረፍት እንዲያደርጉም እንመክራለን፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*